ሰኔ 14 ቀን 2014 ዓ.ም

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት

የተከበሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀፅ 2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 (እንደተሻሻለው 1146/2011) አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 15፤ እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተሰጠው ስልጣን መሠረት መ/ቤቱ ኦዲት ያደረገውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ በኢንቬስትመንት ፕሮጀክት ፋይናንስግ እና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) ፤ የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሰጠውን የበጀት ድጋፍና ድጎማ ተከታታይ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርት፣ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ህጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ፣ ተፈላጊውን ግብ የመታና ውጤት ያስገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገውን የክዋኔና አካባቢ ኦዲት፣ እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ በተደነገገው መሠረት የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትና በተመረጡ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲቶች ዕቅድ ክንውንና የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፤

1. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት እና በኢንቬስትመንት ፕሮጀክት ፋይናንስ (Investment Project Financing) እና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) ተከታታይ እና ማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት ሂሳብ በተመለከተ የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርት፤

2. በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት የተደረጉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ እና በመንግስትና በልማት አጋር ድርጅቶች እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች/ ፕሮግራሞችን ኦዲት ሪፖርት፣

3. የ2013/14 ኦዲት ዓመት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድ ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ የተከናወኑ ልዩ ኦዲት ስራዎች፤ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴን በአጭሩ ያጠቃለለ ነው፡፡

4. የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች፣ በፋይናንስና ሕጋዊነት የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው 8 መ/ቤቶች፣ የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው 39 መ/ቤቶች፣ እንዲሁም የ23 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲት፣ 4 የክትትል ኦዲት ሪፖርቶች፣ 1 ልዩ ኦዲት እንዲሁም 1 ከአለፈው ዓመት ዞሮ የመጣውን በማጠናቀቅ ለም/ቤቱ የቀረቡ ስለሆነ እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡ የሪፖርቶቹም ቅጅ 2 ጥራዞች/የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት እና አጠቃላይ ዘገባ/ እና ሌሎች የተጠቀሱት ሪፖርቶች በሶፍት ኮፒ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤትም እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

5. በዚህ ሪፖርት ውስጥ ተካተው ለተከበረው ም/ቤት የቀረቡት የኦዲት ግኝቶችን በተመለከተ እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ስብሰባ (Exit Conference) ከመደረጉም በላይ ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል፡፡

6. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዓለም አቀፍ የመንግሥት የኦዲት ደረጃዎች፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ሲሆኑ፣ ኦዲቱም የተከናወነው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

<u>የ2013 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ኦዲት ዕቅድና ክንውን</u>

<u>የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ</u>

7. የ2013 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ መሠረት ያደረገው የመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 (1146/2011 እንደተሻሻለው) አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1-15 እና የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001(970/2008 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 63 ንዑስ አንቀፅ 2 ነው፡፡ በየዓመቱ የኦዲት ስራው የሚጀምረው በመጋቢት ወር ሲሆን አስቀድሞ በየካቲት ወር እቅድ በማዘጋጀትና በኦዲት ማኑዋሎች ላይ ስልጠና በመስጠት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሒሳባቸውን መዝጋታቸውን ሳንጠብቅ ኢንትሪም የኦዲት ዘዴን በመጠቀም ኦዲቱን መጋቢት 2013 ዓ.ም በመጀመር ጥር 30/2014 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ታቅዶ ነበር፡፡

8. በዚሁ መሠረት በ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 187 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች 179 መ/ቤቶችና 52 ቅ/ጽ/ቤቶችን በመ/ቤታችን ኦዲት ለማድረግ፤ 8(ስምንት) መ/ቤቶች በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኦዲት

በማስደረግ ተደርሶበት የነበረውን የኦዲት ሽፋን 100% ለማስቀጠል በመጋቢት 2013 ታቀዶ የነበረ ቢሆንም የ6 መ/ቤቶችና የ4 ቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲት በወቅታዊ ሁኔታ፣ ሒሳብ ባለመዝጋትና ቢሮ ባለማቅረብ ኦዲታቸው የተቋረጠ ሲሆን አፈፃፀሙም የ173 መ/ቤቶችና 48 ቅ/ጽ/ቤቶች የህጋዊነት ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርቱ ወጪ የተደረገ በመሆኑ አፈጻጸሙ 96.6% ሆኗል፡፡

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች

9. የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ ኦዲታቸዉ የተጠናቀቀዉን የ171 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የሥራ አመራርና የኦዲት ሪፖርቶች ተዘጋጅተው ለየመ/ቤቶቹ የተላኩ ሲሆን የባለበጀት መ/ቤቶች ሪፖርቶች ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር ከ2011 እና 2012 ካሉት በጀት ዓመታት የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት አስተያየቶች ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ /የተሰጠው የኦዲት አስተያየት/	ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		
	2011	2012	2013
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት	29	10	51
ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው የተገኙ	71	46	73
አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች	5	8	8
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	48	41	39
በጸጥታ ችግር ምክንያት የኦዲት ስራው የተቋረጠ	1	1	4

መግለጫ /የተሰጠው የኦዲት አስተያየት/	ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		
	2011	2012	2013
ሂሳባቸውን በወቅቱ ስላልዘጉ ኦዲት ያልተደረጉ			1
ቢሮ ባለመስጠት ኦዲት ያልተደረጉ			1
ሒሳባቸው ባለመዘጋቱ የሥራ አመራር ሪፖርት ብቻ የተላከና የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠበት	1		
የመውጫ ስብሰባ ያልተደረገ	15	12	2
ድምር	170	118	179

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች

10. መ/ቤታችን ምክር ቤቱ ለ2013 በጀት ዓመት ያጸደቀው በጀት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ባከናወነው ኦዲት በርካታ የሂሳብ አያያዝ ግድፈቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከህግና ከተዘረጋው አሠራር ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች የተገኙ ሲሆን፣ የም/ቤቱን ትኩረት ሊያገኙ የሚገቡ አንኳር ግኝቶች ብቻ ተለይተው እንደሚከተለው ቀርበዋል::

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

11. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝና አጠባበቅን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,491,901.91 እና ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 21,749.54 በድምሩ ብር 1,513,651.45 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡

12. በተጨማሪም በ3 መ/ቤቶች በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ብር 632,044.97፣ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 241,244.00 እና በቀብሪድሃር ዩኒቨርስቲ ብር 128,030.00 በድምሩ ብር 1,001,318.97 በክፍያ መመሪያ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ወጪ የተደረገ ሂሳብ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡ በሌላም በኩል በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ባለበጀት መ/ቤቶች ያልተጠቀሙበት ጥሬ ገንዘብና በባንክ የሚገኝ ገንዘብ ለገንዘብ ሚኒስቴር ፈሰስ ሊያደርጉ የሚገባ ቢሆንም በወራቤ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለረጅም ዓመታት ፈሰስ ሳይደረግ በባንክ ውስጥ የተጠራቀመ የገቢ ሂሳብ ብር 87,909,298.90 ተገኝቷል፤ እንዲሁም ከጉድለት ተሰብሳቢ (cash shortage) በሚል የሂሳብ መደብ መያዝ ሲገባው በእጅ በቆጠራ ሳይታይ በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ ተብሎ እየተንከባለለ የመጣ በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 1,134,396.95 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡

13. በጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳቦች ላይ ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ብክነትና ጉድለት የሚያጋልጥ በመሆኑ፣ በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተገቢው እርምጃ ተወስዶ እንዲተካ እንዲሁም የታዩት የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዲስተካከሉና ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

<u>**የውዝፍ ተሰባሳቢ ሂሣብ**</u>

14. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳዳር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 በተደነገገው መሠረት የሰነድ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ ሲጣራ በ133 መ/ቤቶች እና በ26 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 13,100,235,836.20 እና በ4 መ/ቤቶች ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ ብር 10,183,865.34 በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በ6 መ/ቤቶችና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 106,841,610.27 ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

15. በ2012 በጀት ዓመት በ90 መ/ቤቶችና በ12 ቅ/ጽ/ቤቶች የነበረው ብር 7,480,256,624.50 በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ ያለባቸው መ/ቤቶች ቁጥር በ43 መ/ቤቶችና 14 ቅ/ጽ/ቤቶች የጨመረ ሲሆን ከገንዘብ አንፃርም በብር 5,619,979,211.70 ወይም 75% ጨምሮ ተገኝቷል፡፡

16. በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ከፍተኛውን ድርሻ ከያዙት መካከል፡- የጤና ሚኒስቴር ብር 4,084,077,060.81፣ የብሔራዊ አደጋ ስጋትና ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 1,938,670,820.47፣ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 1,019,438,243.64፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 428,571,375.86፣ የጂግጂጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 421,584,874.70 እና የቀድሞው ውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ብር 378,032,951.96 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

17. በወቅቱ ያልተወራረደው ተሰብሳቢ ሂሳብ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 1,492,293,352.82 ፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 7,564,109,438.36፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 1,474,128,360.27 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 46,097,914.20 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 2,523,606,770.55 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት ያልተቻለ ነው፡፡

18. በየመ/ቤቱ እየታዩ ያሉት ተሰብሳቢ ሂሳቦች እየጨመሩ መሄድና በወቅቱ አለመወራረድ በቆይታ ብዛት ገንዘቡን ያለመሰብሰብ ዕድሉን ያሰፋዋል፡፡ በመሆኑም መ/ቤቶች ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣቦቹን ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ተከታትለው ገንዘቡን እንዲሰበስቡ ወይም እንዲያወራርዱ፣ ማስረጃ ያልተገኘለትን ተሰብሳቢ ሂሳብ በተመለከተ ጉዳዩ ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ እንዲወራረድ እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>የገቢ ሂሣብ</u>

19. የመንግሥት ገቢ በወጡት ሕጎች መሠረት በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝቷል፡፡

<u>በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ</u>

20. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መ/ቤቶች እና በስራቸው ባሉ 21 ቅርንጫፍ

ጽ/ቤቶች የንግድ ትርፍ ግብር፤ የገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/፤ ቅድመ ግብር (withholding tax) እና የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ብር 374,159,232.52 እና በሌሎች በ32 መ/ቤቶች ብር 36,735,525.48 በድምሩ ብር 410,894,758.00 ገቢ ለመሰብሰብ በሚያስገድዱ አዋጆችና ደንቦች መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ ተገኝቷል፡፡

21. በደንቡ መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በጉምሩክ ኮሚሽን የቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብር 237,420,564.38፣ የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 23,574,371.23፣ በገቢዎች ሚኒስቴር፡- የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ብር 72,396,669.64፣ የባህርዳር ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ብር 7,095,646.51, ምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 6,316,978.41 እና የቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 6,201,379.80 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

22. በመሆኑም መ/ቤቶቹ ለወደፊቱ የመንግሥትን ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው እና በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>መሰብሰብ ሲገባው ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ ቅጣት</u>

<u>እና ውል ማስከበሪያ ሂሳብ</u>

23. በፌዴራል መንግሥት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4 (ሀ) እና (ለ) መሠረት አቅራቢው ሣይፈጽም በቀረው የውል መጠን ላይ ውል ሰጪ የመንግሥት መ/ቤቶች በየቀኑ 0.1% ወይም 1/1000ኛ ከውሉ ዋጋ 10% ሣይበልጥ የጉዳት ካሣ ሊሰበስቡ እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ በዚህ መሠረት በ9 መ/ቤቶች ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ ብር 21,628,973.63፣ በ4 መ/ቤቶች የህንጻ ስራ ተቋራጮች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ያልተሰበሰበ ውል ማስከበሪያ ብር 21,972,027.98 በኦዲቱ ተገኝቷል፡፡

24. የጉዳት ካሳ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል፡- የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 12,433,614.49 እና መቱ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,907,003.36 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ የውል ማስከበሪያ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል የአሶሳ ዩኒቨርስቲ

ብር 14,770,258.07 እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,226,798.77 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

25. በተጨማሪም መንግስት ወጪያቸውን ሸፍኖላቸው ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ተልከው የተማሩ ሰራተኞች በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው መሰብሰብ የነበረበት የትምህርት ክፍያ በ3 መ/ቤቶች ብር 1,973,328.00 ገቢ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

26. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በመንግሥት መመሪያና በገቡት ውል መሠረት እስከ አሁን ያልተሰበሰበውን የጉዳት ካሣና ሌሎች ገቢዎች እንዲሰበስቡና ለወደፊቱም መመሪያው በሚጠይቀው መሠረት እንዲፈጽሙ አሳስበናል፡፡

ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

27. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎች ሚኒስቴር ስር ባሉት 9 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በጉምሩክ ኮሚሽን ስር ባሉት 10 ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ኦዲት/በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ውሳኔ መሰረት ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ ብር 9,456,736,435.78 እና በ3 መ/ቤቶች ከውዝፍ ያልተሰበሰበ ብር 70,803,191.09 በድምሩ ብር 9,527,539,626.87 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

28. የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና የአገር ውስጥ ግብር እና ታክስ በወቅቱ ውዝፍ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች፡- በገቢዎች ሚኒስቴር የምዕራብ አዲስ አበባ አ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት ብር 1,917,614,281.68፣ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 1,538,579,228.76፣ የከፍተኛ ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት ብር 1,090,039,680.34 እና በጉምሩክ ኮሚሽን የቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,299,648,470.11፣ ሞጆ ቅ/ጽ/ቤት ብር 596,145,393.68፣ ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 246,555,809.69 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

29. በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት የሚያከናውናቸውን ማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት አገልግሎቶችን ለማስፋፋትና መሠረተ ልማት ለመዘርጋት ወሳኝ ሚና

የሚኖረው በመሆኑ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ

30. በበጀት ዓመቱ ገቢን እንዲሰበስቡ በተፈቀደላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች ብር 175,418,886.64 የገቢ ሂሳብ ያልመዘገቡና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ ሆነው ተገኝቷል፡፡

31. የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ካላካተቱ መ/ቤቶች መካከል፡- ጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 93,546,750.55፣ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 36,831,811.45፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 16,749,006.84፣ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 16,690,944.18 እና ጂንካ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,009,460.05 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

32. በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ማንኛውንም የመንግስት ገቢ ሕጋዊ በሆነ መንገድ በመሰብሰብ እንዲመዘግቡና በሂሳብ መግለጫዎቻቸው በማካተት ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያደርጉ እና እንዲጠቀሙበት በሕግ ያልተፈቀደላቸውን ገቢ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት

የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

33. የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ7 መ/ቤቶች ከተለያዩ ገቢዎች የተሰበሰበው ገቢ ብር 154,406,678.78 አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ባለመሟላታቸው የገቢውን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

34. በሌላ በኩል 72 ድርጅቶች ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር፤የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ኤክሳይስ ታክስና ተርንኦቨር ታክስ በወቅቱ ያላሳወቁ መኖራቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

35. ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች ዝርዝር በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ፤ ግብር ከፋዮች የሚፈለግባቸውን ግብር በሙሉ በወቅቱ አሳውቀው እንዲከፍሉ ተገቢውና ጥብቅ ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የወጪ ሂሣብ

36. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች እንዲሁም በግዢ አዋጅና መመሪያ መሠረት በአግባቡ ወጪ ማድረጋቸውና መጠቀማቸውን፣ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡንና ሂሣቡም በትክክል መመዝገቡንና ሪፖርት መደረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሣብ

37. በወጪ ለተመዘገቡ ሂሣቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ41 መ/ቤቶች እና በ1 ቅ/ጽ/ቤት የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 139,723,599.47 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

38. ማንኛውም ሂሣብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንቡና መመሪያዎች መሠረት ወጪውን የሚደግፉ ማስረጃዎች መሟላታቸው እንዲረጋገጥ፣ ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉና ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

39. ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈጸሙ ሲጣራ በ87 መ/ቤቶችና በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 89,238,375.07 ከደንብና መመሪያ ውጭ ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

40. ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡- ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 12,205,748.26፣ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,351,862.00፣ እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ

ብር 7,097,200.00፣ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,949,923.38 ፌደራል አነስተኛ እና መካከለኛ ማኒፋክቸሪንግ እንዱስትሪ 4,916,972.78 እና የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,636,820.12 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

41. በተጨማሪም በ16 መ/ቤቶች እና በ1 ቅ/ጽ/ቤት በመስሪያ ቤቱ ለሌሉና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ ብር 341,382.95፣ በ18 መ/ቤቶች ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር የተፈጸመ ክፍያ ብር 77,855,816.20 እና በ12 መ/ቤቶች በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይፈቀድ ብር 30,743,565.54 የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተከፍሎ ተገኝቶል፡፡

42. በ18 መ/ቤቶች ደግሞ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር ብር 16,557,888.09 የተፈጸሙ ክፍያዎች እና በ8 መ/ቤቶች የግብር መቀጫ፣ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በወቅቱ ባለመክፍሉ ምክንያት አላግባብ የተከፈለ የወለድ ቅጣት 2,807,314.21 ክፍያ ከመንግስት ካዝና ወጪ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

43. በመሆኑም ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ የተከፈለው ሂሣብ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግና ክፍያውን ካፀደቁትና የፈፀሙ አካት ተጠያቂ እንዲደረጉ፣ እንዲሁም የክፍያ ስርዓት ለሌላቸው ሥርዓቱን በመዘርጋትና በማስፈቀድ ለወደፊቱ ደንብና መመሪያዎች ተከብረው መሰራት እንዳለበት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች አሳስበናል፡፡

በብልጫ የተከፈለ ወጪ

44. በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሰረት በአግባቡ የተከናወኑ፣ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸሙ ክፍያዎች ስለመሆናቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፣ በ47 መ/ቤቶች እና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 31,960,542.84 እና ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 10,677,649.53 በጠቅላላው ብር 42,638,192.37 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

45. ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ ከህግ ውጪ ከመሆኑም በላይ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግና ለሙስናም በር የሚከፍት አሠራር ነው፡፡ በብልጫ

ከአዋጅ፣ ከደንብና ከመመሪያ በላይ የተከፈሉት ክፍያዎች ከሚመለከታቸው ላይ ተመላሽ እንዲደረጉ እና እነዚህን ወጪዎች ያዘዙ ኃላፊዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ አሳስበናል፡፡

የግዥ አዋጅና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዥዎች

46. የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት የግዢ አዋጅና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ37 መ/ቤቶችና በ3 ቅ/ጽ/ቤቶች ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ በመፈጸም ብር 372,417,530.77፣ በ9 መ/ቤቶች መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ ብር 25,320,374.66፣ በ29 መ/ቤቶች ግልጽ ጨረታ መውጣት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ ብር 73,882,975.94፣ በ24 መ/ቤቶች እና በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ ብር 19,546,986.53 እና በ28 መ/ቤቶችና በ5 ቅ/ጽ/ቤቶች ሌሎች የግዥ ሂደት ሳይከተሉ ብር 92,709, 795.13 በድምሩ ብር 583,877,663.03 የመንግሥት የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

47. ከግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፡- ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 73,028,431.03፣ የሰላም ሚኒስቴር ብር 61,063,450.32 ጂንካ ዩኒቨርሲቲ ብር 49,493,614.66፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 29,701,889.18፣ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 26,524,332.91 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

48. የግዥ መመሪያን ሳይከተሉ ግዥ መፈጸም የህግ ጥሰት ከመሆኑም በላይ መንግሥት ተወዳዳሪ ዋጋ እንዳያገኝ እና ለጥራት መጓደል የሚያጋልጥ በመሆኑ የመንግሥት ግዥ አዋጅና መመሪያን አክብረው እንዲሰሩ ያላከበሩ አካላት ተጠያቂ እንዲደረጉ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ንብረቱ ገቢ ስለመሆኑ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

49. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ7 መ/ቤቶች በብር 3,273,178.26 ተገዙ ተብሎ ለተከፈለው ሂሳብ ንብረቱ

ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በ1 መ/ቤት ብር 449,588,466.02 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀርበላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

50. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የሚገዛው ማንኛውም ንብረት የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ተዘጋጅቶለት ለመ/ቤቱ ገቢ ተደርጎ ቁጥጥር ካልተደረገ የመንግሥትና የህዝብ ንብረትና ገንዘብ በቀላሉ ለብክነትና ለሥርቆት ሊዳረግ ይችላል፡፡

51. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁ፣ ቀረጥ ተከፍሎ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥ የተከፈለውን ሒሳብ በተመለከተ ጉዳዩ ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

<u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው</u>

<u>በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ</u>

52. በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ9 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች ክፍያ በድምሩ ብር 10,095,985.09 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዘግቦ ተገኝቷል፡፡

53. የቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,799,901.49 እና የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንን ብር 997,500.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

54. ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለባቸው፡፡

55. በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብለት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና

ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ የወጪ ሂሳብ

56. በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸውና ትክክለኛ ወጪ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ22 መ/ቤቶች ብር 4,083,767,784.26 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

57. ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፡- ብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 3,850,272,193.66፣ የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 171,688,892.19፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ብር 19,651,132.67፣ ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,991,230.78 እና የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ብር 1,335,879.59 ዋና ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

58. ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብ የመንግሥትን ገንዘብ ወጪ ማድረግ ህግና አሠራርን መጣስ ከመሆኑም በላይ የህዝብንና የመንግሥትን ገንዘብ ለጥፋትና ለብክነት የሚዳርግ በመሆኑ ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ ሆኖ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ በቂ ማስረጃ እንዲቀርብለት፣ አለበለዚያ ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

59. መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም የመንግስት የግዥ ህግን ጠብቆ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ከታዩ 7 መ/ቤቶች ብር 6,729,403.09 ብክነት መኖሩ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ከተጠቀሱት ምክንያቶች መካከልም የነዳጅ ካርድ ገቢ ያልተደረገ፣ የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ያልቀረበ በመሆኑ የወጣውን የነዳጅ በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ ያልተቻለ እና ሌሎች ምክንያቶች ናቸው፡፡

60. በመሆኑም መንግስት በከፍተኛ ውጭ ምንዛሬ ለነዳጅ የሚያወጣውን ገንዘብ አላግባብ መጠቀም በሀገር ላይ የሚያመጣው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ መ/ቤቶች

የነዳጅ አጠቃቀም ስርዓታቸው ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲያደርጉ እና የባከነው ገንዘብም ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የተከፋይ ሂሣብ በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

61. በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን እና ሂሳባቸውም በተከፋይ መያዝ የሚገባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ87 መ/ቤቶችና በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 945,455,650.97 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ ከተጠቀሰው ተከፋይ ሂሳብ በተጨማሪ በ9 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 223,231,147.79 በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበ ቢሆንም ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፤ እንዲሁም በተከፋይ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶች ብር 2,653,944.70 በኦዲቱ ተገኝቷል፡፡

62. በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች መካከል፡- የሰላም ሚኒስቴር ብር 263,169,664.85፣ የኢኖቬንሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 131,833,508.57፣ የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 63,837,450.31፣ አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 45,473,305.97 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እንዲሁም የተከፋዩን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለባቸው መ/ቤቶች መካከል፡- የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 172,078,190.32 እና በጉምሩክ ኮሚሽን ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 21,995,168.30 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

63. የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ ቆይታው ሲተነተን፡- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 140,768,936.57፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 157,578,161.69፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 59,036,631.79 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 54,589,604.97 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 533,482,315.95 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ያልተለየ ሂሳብ ነው፡፡

64. በመሆኑም የተመለከተው ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ ተጣርቶ በፋይናንስ ሕጉ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲከፈል፤ ትክክለኛነቱን ማጣራት ያልተቻለውም ተከፋይ ሂሳብ ዝርዝር ማስረጃ በጥንቃቄ ተጣርቶ ማስረጃ እንዲቀርብ አሳስበናል፡፡

የበጀት አጠቃቀም

ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ

65. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ24 መ/ቤቶች በልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱና በጀት ሳያዛውሩ ከመደበኛ በጀት ብር 398,849,289.36፣ ከውስጥ ገቢ ብር 2,416,272.06 እና ከካፒታል በጀት ብር 243,933,366.02 በድምሩ ብር 645,198,927.44 ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

66. ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ ከተጠቀሙ መ/ቤቶች መካከል፡- የኢትዮጵያ ቴክኒካል ዩኒቨርስቲ ብር 253, 814,174.36፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 159,474,595.88፣ ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 47,651,241.08፣ ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ብር 31,419,378.72፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 28,967,241.05፣ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 26,565,165.59 እና ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ 25,808,529.63 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

67. በጀት ሳይፈቀድ ወይም ዝውውር ሳይደረግ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንደዚሁም በበጀት አዋጁ መሠረት የተከለከለ በመሆኑ መ/ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ የተፈቀደላቸውን አሠራር በመከተል በተገቢው መንገድ የበጀት ዝውውር በማድረግ አስፈቅደው ሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

68. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ መጠቀመቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% በላይ ያልተጠቀሙበትን ብቻ በመውሰድ በ144 መ/ቤቶች እና በ13 ቅ/ጽ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 5,887,545,730.64 ፣ የውስጥ ገቢ ብር 155,694,107.26 እና ካፒታል ብር 14,969,539,035.77 በድምሩ ብር 21,012,778,873.67 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡

69. ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፡- የቀድሞው የመስኖ ልማት ኮሚሽን ብር 6,237,628,372.23፣ የቀድሞው የውሃ ልማት ኮሚሽን ብር 1,118,564,482.36፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 887,189,898.27፣ የቀድሞው የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ብር 648,139,687.58፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 560,234,919.32፣ ብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮምሽን ብር 465,877,845.38 እና ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሚኒስቴር ብር 423,469,538.09 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

70. በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል፣ እንዲሁም መንግስት ለሌላ ልማት እንዳይጠቀምበት የሚገድብ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ በበጀት ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እና የማይጠቀሙበትን በጀት ለገንዘብ ሚኒስቴር ቶሎ ማሳወቅ እንዳለባቸው ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የንብረት አስተዳደር</u>

71. በየዓመቱ በምንሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሠረት በርካታ መ/ቤቶች የንብረት አስተዳደራቸውን ለማሻሻል ጥረት እያደረጉ ቢሆንም አሁንም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ይታያሉ፡፡ በዚህ ረገድ በ2013 በጀት ዓመት ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች፡-

ተ.ቁ	የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
1	ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	24	
2	ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	13	1
3	የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	16	
4	ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	15	2
5	የአላቂ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ ስቶክ/ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላደረጉ መ/ቤቶች	22	

ተ.ቁ	የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
6	ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	80	1
7	አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	111	19
8	ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	33	
9	በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	17	
10	የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ያላረጋገጡ፣	3	
11	የንብረት ጥበቃ ላይ ተመድበው ተያዥ/ዋስትና ያላቀረቡ ሰራተኞች	1	
12	የተተዉ፣ የተወረሱ እና ያልተወረሱ በህግ ሂደት ላይ ያሉ ንብረቶች አስተዳደር እና ቁጥጥር ያላደረጉ ቅ/ጽ/ቤቶች		10
13	ከመ/ቤቱ የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ ያላደረጉ መ/ቤቶች	26	2
14	ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	16	
15	ቋሚ ንብረት በቋሚ መዝገብ ላይ ያልመዘገቡ እና በቋሚ ንብረት በቆጠራ ሪፖርት ያልተካተቱ መ/ቤቶች	1	

ተ.ቁ	የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
16	የጸደቀ መመሪያ ሳይኖር ተላልፈው ስለተሰጡ መኖሪያ ቤቶች	1	
17	የእንስሳት መድሀኒት ለአርሶ አደሮች በትክክል ለተጠቃሚዎች መድረሱን ማረጋገጥ ያልተቻለ መ/ቤቶች	1	
18	የቋሚና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ የተቀመጡባቸው መ/ቤቶች	4	
19	በእርዳታና በስጦታ ለተገኙ ዕቃዎች ዋጋ ያልተመኑ መሥሪያ ቤቶች፤	3	2
20	ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም በቆጠራዉ ያልተካተቱ ንብረቶች ያሉባቸው	1	
21	የንብረት ምዝገባ በኢፍሚስ ሲስተም እንዲመዘገብ ያላደረጉ መሥሪያ ቤቶች፤	3	
22	የአገልግሎት ግዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች በስቶር የሚገኝባቸው መ/ቤቶች (መጠኑ ያልተገለጸ)	2	
23	የመጽሃፍት ውሰት ጊዜያቸውን ጠብቀው ተመላሽ የማያደርጉ መ/ቤቶችን በተመለከተ (መጠኑ ያልተገለጸ)	1	
24	በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ለቢሮ አላማ የተሰራን ህንፃ ለመኖርያ ቤት ያዋሉ	1	
25	የግዢ እቅድ የሌላቸው	1	
26	ያለምንም መረካከቢያ በግለሰብ ስም ተይዘው በአደራ የተቀመጡ ንብረቶች ያሉባቸው	1	
27	የዕቃ ግምጃ ቤት ሰራተኛ የሌለው	1	

ተ.ቁ	የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
28	የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት መስራት አለመስራቱ የማይረጋገጥ ፤	1	
29	በንብረት ክፍል (እስቶር) ውስጥ ተመላሽ የሚደረጉ ንብረቶች አዲስ ተገዝተው ከሚገቡ ንብረቶች ተለይተው የማይቀመጡባቸው መ/ቤቶች	2	

መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

72. በመሆኑም የየመሥሪያ ቤቶቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም አዋጅ ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲመራ፣ በታዩት ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ፣ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ</u>

73. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ጉድለቶች ታይተዋል፡፡

ተ.ቁ	የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች/ቅ*	መኪና	ሞተር ብስክሌቶች/**
1	ሊብሬ ያልቀረበላቸው	21/3	72/5	40/42
2	በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆሙ	64/4	612/27	53/17
3	የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው	4/2	5	9/4
4	የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	39/4	431/19	2

ተ.ቁ	የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች/ቅ*	መኪና	ሞተር ብስክሌቶች/**
5	የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው/ጌጅ/ የማይሰራ	11	75	6
6	የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው/የማያደረጁ (በተወሰኑ መ/ቤቶች በቁጥር ያልተገለጸ መኖሩ)	10/1	157	
7	ታርጋቸው ኢ.ት ያልሆነ	3	8	4
8	ሊብሬው ብቻ ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ	1	1	
9	ሻንሲ ቁጥር የሌላቸው	1	1	
10	የሞተር ቁጥር የሌላቸው	1	1	
11	የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት	6	7	
12	አገልግሎት የማይሰጡ/መወገድ/ ያለባቸው ተሽከርካሪዎች	4	13	
13	የመኪና የሞተር ቁጥር ማረጋገጥ ያልተቻለ	1	1	
14	የብቃት ማረጋገጫ/የቴክኒክ ምርመራ ያላደረገ	1		3
15	የተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ መዝገብ ላይ የተሽከርካሪዎች ዋጋ ያልተገለጸ	1	5	

ቅ*- ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

**- ሌሎች- ሎቤድ፤ ትራክተር፤ ባጃጅ

መኖራቸው ታውቋል፡፡

74. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በተዘረዘሩት የቁጥጥር ድክመቶች ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው፣ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ፣ ሊብሬ ያልቀረበላቸው አስፈላጊው ማስረጃ ተሟልቶ እንዲወጣላቸው ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

የኢንቨስትሜንት ፕሮጀክት ፋይናንስንግና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም በተመለከተ

75. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት በየሩብ ዓመቱ የኢንቨስትሜንት ፕሮጀክት ፋይናንስንግ እና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የአገልግሎቱ አቅራቢ በሆኑት በወረዳና በክልል ደረጃ በሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክተሮች እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ኦዲት ሪፖርቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተልኮ ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

76. በዚሁ መሰረትም ከክልሎች በናሙና በተመረጡ ወረዳዎች ፣ የፕሮግራሙ ፈጻሚ በሆኑ የከተማ አስተዳደር፣ የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ በሆኑ የክልል ሴክተር ቢሮዎች 236 የተከታታይ፣ 58 የማረጋገጫ (Verification) እና 1 ዓመታዊ ማጠቃለያ ጠቅላላ ድምር 295 ኦዲቶችን ለመሥራት በእቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን አፈጻጸሙ 259 የተከታታይ ኦዲት፣ 60 የማረጋገጫ (Verification) 1 ዓመታዊ ማጠቃለያ እና 3 ልዩ ኦዲትን ጨምሮ በጠቅላላ ድምር 323 (109.4%) የኦዲት ስራዎችን በማከናወን ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ተልኳል፡፡

የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትን በተመለከተ

77. የገንዘብ ሚኒስቴር የ2013 በጀት ዓመት የተጠቃለለ የወጪ፣የገቢ፣ የእርዳታና የብድር ሒሳቦች የኦዲት ስራው ተጠናቆ ሪፖርቱ ለሚላክላቸው አካላት ተልኳል፡፡

የተከበሩ አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

<u>የክዋኔ ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና ግኝቶችን በተመለከተ</u>

78. መ/ቤታችን ከፋይናንስና የሕጋዊነት (Regularity) ኦዲት በተጨማሪ በክዋኔ ኦዲት ላይ ትኩረት ለማድረግ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች፤ እንዲሁም ለተልዕኮ ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ ማሳካታቸውን እና የአካባቢ ጥበቃና የዘላቂ ልማት ግቦችን ሊያሳካ በሚችል መልኩ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ በመጋቢት 2013 ተጀምረው እስከ ጥር 30/2014 የሚጠናቀቁ 25 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችና አንድ የዞረ እና 4 የክትትል ኦዲቶችን ለማከናወን በድምሩ 30 ኦዲቶችን በእቅድ ተይዘው ነበር፡፡

79. በዚህም መሠረት አንድ የዞረውና 24 አዲስ ክዋኔ ኦዲቶች እና 4 የክትትል ኦዲቶች በድምሩ የ29 ክዋኔ ኦዲቶች ሥራ በታቀደው መሠረት ተጠናቅዋል፡፡ አንድ የክዋኔ ኦዲት በዝርዝር ኦዲት ላይ የሚገኝ በመሆኑ በአመቱ የክዋኔ ኦዲት የእቅድ ክንዉን 96.7% ሆንዋል፡፡ የተጠናቀቁት ሪፖርታቸው ለም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት ተልክዋል፡፡ ከተሰሩት የክዋኔ ኦዲቶች ዉስጥ ሰባቱ አካባቢ ኦዲት ላይ ያተኩሩ ሲሆን፤ በኦዲቱ የታዩና የምክር ቤቱ ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ግኝቶቹ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ በአዳማ የግብርና ማሽነሪ ማምረቻ የስራ አፈጻጸም ዉጤታማነትን በተመለከተ

80. የአዳማ የግብርና ማሽነሪ ማምረቻ ኢንዱስትሪ የምርት ግብዓት ግዥ ለማከናወን የሚያስችል ቀልጣፋ እና መመሪያን የተከተለ የግዥ ስርዓት መዘርጋት ቢገባዉም ኢንዱስትሪው ያለምንም የግዥና የገበያ ፍላጎት ጥናት፣ የፈጸማቸዉ ግዥዎች የግብርና ማሽነሪዎች ከኢትዮጵያ መልከዓ-ምድርና የአፈር ሁኔታ ጋር የተገናዘበ እና የተስማሚነት ጥናት ሳያካሂድ እንዲሁም ያለምንም የግዥ ጨረታና ዕቅድ ከተለያዩ ሀገሮች በቁጥር ከ14,452 (አስራ አራት ሺህ አራት መቶ ሀምሳ ሁለት) በላይ የሚሆኑ የተለያየ የፈረስ ጉልበት ያላቸውን ትራክተሮችን ከ2003 እስከ 2007 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ማለትም 146,134,400 (አንድ መቶ አርባ ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ አራት ሺ አራት መቶ) የአሜሪካን ዶላር (USD) እና 10,513,431.20 (አስር ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሦስት ሺ አራት መቶ ሰላሳ አንድ ከሀያ ሳንቲም) ዩሮ (EURO) በማውጣት አጠቃላይ በወቅቱ በነበረው የምንዛሬ ዋጋ 4,837,853,383.97 (አራት ቢሊዮን ስምንት መቶ ሰላሳ ሰባት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሀምሳ ሦስት ሺ ሦስት መቶ ሰማኒያ ሶስት ከዘጠና ሳባት ሳንቲም) ብር ወጪ በማውጣት የግብርና ማሽነሪዎችን ግዥ የፈፀመ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት የካቲት 2014 ዓ.ም ድረስ **ከ5,825 (አምስት ሺ ስምንት መቶ ሀያ አምስት)** በላይ የሚሆኑት አገልግሎት መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ እና ሳይሸጡ ተከማችተዉ የሚገኙ መሆኑ፣

81. ኢንዱስትሪው ከተመሰረተ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ቢሆንም እስካሁን የግብርና ማሽነሪ ምርቶችን የሚያዘምኑና የሚያሻሽሉ የምርምርና ጥናት ስራዎችን በማከናወን እንዲሁም በዘርፉ ከተሰማሩ ኩባንያዎች ጋር በቅንጅት በመስራት የዘርፉን የቴክኖሎጂ አቅም ለማሳደግ ወይም ለማሻሻል ያልሰራ መሆኑ፤

82. ኢንዱስትሪው ለሚያመርታቸው የግብርና ማሽነሪዎች ጥራት ስታንዳርድ ወይም ደረጃ ያለዘጋጀ መሆኑንና ያለምንም የጥራት መለኪያ ወይም ስታንዳርድ ከውጭ ሀገር በጅምላ የገቡ የግብርና ማሽነሪዎችን የጥራት ደረጃቸው ሳይረጋገጥ በዘልማድ በከፊል እየተገጣጠሙ ለገበያ የሚቀርቡበት አሰራር አሁንም የቀጠለ መሆኑ፤

83. ኢንዱስትሪው የግብርና ማሽነሪዎችን ከመገጣጠም ቴክኖሎጂ ወደ ማምረት ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያድግበትን ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ቢገባውም እስካሁን ኢንዱስትሪው የአምራችነት ስያሜን ከመያዝ ውጭ ምንም ዓይነት የግብርና ማሽነሪዎችን በራሱ የማያመርትና ይሄንን ለማከናወን የሚያስችል በቂ ማሽን የሌለው ከመሆኑም በላይ ከተመሰረተ ከ40 ዓመት በላይ እድሜ ያስቆጠረ የትራክተር መገጣጠሚያ ፋብሪካ ቢሆንም አሁንም በመስራት ላይ የሚገኘው ከውጭ ሀገር የግብርና ማሽነሪዎችን በማስመጣትና በከፊል የትራክተር አካላትን የመገጣጠም ስራ ብቻ መሆኑ፤

84. ኢንዱስትሪው የሽያጭ ሂሳቦችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ወጥ የሆነ ስርዓትና አሰራር በመዘርጋት የሽያጭ ሂሳቦችን በአግባቡ መሰብሰብ ቢጠበቅበትም ብር 2,118,012,191.35 (ሁለት ቢሊዮን አንድ መቶ አስራ ስምንት ሚሊዮን አስራ ሁለት ሺ አንድ መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም) ሳይሰበሰብ የቀረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

85. ኢንዱስትሪው ውጤታማ የብድር አመላለስ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ቢገባውም ብር 1,961,684,854.4 (አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ስልሳ አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማኒያ አራት ሺ ስምት መቶ ሀምሳ አራት ብር ከአራት ሳንቲም) መክፈል የነበረበት የተጠራቀመ ዕዳ ወይም ተከፋይ ሂሳብ ያልከፈለ መሆኑ፤

86. ኢንዱስትሪው ከ1.2 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የመስኖ ፕሮጀክቶችን በአፋር፣ በሶማሌ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልሎች ኮንትራት የወሰደ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጥር 2014 ዓ.ም ድረስ አንዳቸውንም የመስኖ ፕሮጀክቶች አጠናቆ ያላስረከበ መሆኑንና ሁሉም ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ሳይጠናቀቁ በጅምር የቀሩ መሆኑ፤በኦዲቱ ታይቷል ፡፡

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የፕሮጀክቶች ግንባታ አፈፃፀምን በተመለከተ

87. ኮርፖሬሽኑ የአዳማ—አዋሽ መንገድ ከባድ ጥገና እና መንገዱን ለ10 ዓመት ለማስተዳደር ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር (የቀድሞው መንገዶች ባለሥልጣን) መንገዱን ሊያስተዳደር እና በአካባቢ ያሉ ሀብትና ንብረት ጥበቃና እንክብካቤ

ለማድረግ ዉል የገባ ሲሆን፤ በውሉ መሰረት ግዴታዉን ባለመወጣቱ በሁለት ወር ብቻ የሰኔ እና የሀምሌ 2013 ዓም. 39.8 ትሪሊዮን ቅጣት እንዲከፍል የተጠየቀ መሆኑ፤ የተጠየቀው ክፍያ ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት የካፒታል መጠን እጅግ የበለጠ ሲሆን ይህ ዉል እንደገና ታይቶ ካልተስተካከለ ወይም እልባት ካልተገኘለት ኮርፖሬሽኑ የመፍረስ አደጋ ሊጋረጥበት ስለሚችል በአስቸኳይ እልባት እንዲሰጥበት አሳስበናል፡፡

88. ኮርፖሬሽኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 366/2008 መሰረት በአዋጅ የተፈቀደለት ካፒታል ሊያሳድግ በተለያየ ምክንያት በአይነት ወደ ሌላ አካል የተሸጋገሩ በገንዘብ እና በአይነት የተመዘገቡት ሀብቶች ከኮርፖሬሽኑ ሂሰብ መዝገብ ሊሰረዙ እና ማካካሻ ካፒታል ሊደረግለት ይገባል፡፡

89. ይሁን እንጂ ለኮርፖሬሽኑ መቋቋሚያ ካፒታል አካል ተደርገው በአይነት የተሰጡ በፌዴራል መንግስት የተገነቡ ግድቦችንና የውሃ ውቅሮችን የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ “መ” መሠረት ባለቤትነታቸው ለውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር እንዲተላለፉ ሲወሰን በህግ የተወሰነላቸው ግድቦችና የውሃ ውቅሮች የገንዘብ መጠናቸው ተሰልተው ከኮርፖሬሽኑ መቋቋሚያ ካፒታል ላይ ያልተቀነሰ መሆኑ ፣ በአዋጁ መሰረትም ከተላለፈለት ሚ/ር ርክክብ ያለፈጸመ መሆኑ

90. በተጨማሪም የኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የተወሰኑ ዲስትሪክቶች እና ንብረቶች እስከ ሐምሌ 20/2012 ዓ.ም ርክክቡ መጠናቀቅ እንደለበት የተገለፀ ቢሆንም እስከ ጥቅምት 30/ 2014 ዓ.ም ርክክቡ አለመጠናቀቁ እና የተዛዋወሩት ካፒታል መጠን ግምት ተሰርቶ ከኮርፖሬሽኑ ካፒታል ላይ አለመቀነሱ፤ መንግስት ወደ ሌላ አካለት እንዲዘዋወሩ በወሰነባቸዉ ካፒታሎች ምትክ ማካካሻሻ ካፒታል አለመመደቡ ታውቋል፡፡ በሌላም በኩል ኮርፖሬሽኑ የተለያየ ስራዎችን የሰራበት ብር1,063,543,204.86 መሰብሰብ ቢገባዉም ያለሰበሰበ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታይቷል፡፡

በቀድሞዉ የፌደራል የተቀናጀ የመሠረተ ልማቶች ማስተባባሪያ ኤጀንሲ የግንባታ፣ መሥመር ዝርጋታ እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ሥራዎች (መንገድ፣ ውሃ፣ መብራት ወዘተ...) አፈፃፀምን በተመለከተ

91. ኤጀንሲው በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 857/2006 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሀገራዊ የተቀናጀ መሰረተ ልማት መሪ ፕላን (ማስተር ፕላን) ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በመተባበር ሊያዘጋጅና በሚመለከተው አካል ሊያፀድቅ ይገባል፡፡ ነገር ግን ከተለያዩ ተቋማት በኦዲቱ በታየዉ፤

- ✓ ኤጀንሲው ሃገራዊ የተቀናጀ መሰረተ-ልማት መሪ ፕላን ማዘጋጀት ቢገባውም አለማዘጋጀቱ፣
- ✓ በ2012 ዓ.ም በኤጀንሲው በተዘጋጀው የተቀናጀ የእቅድ ዝግጅት ትግበራ ማእቀፍ ሰነድ ላይ የመሰረተ ልማት ተቋማት መስመሮቻቸውን ሲዘረጉ በከተሞች የተዘጋጁ ማስተር ፕላን ላይ የተካተቱትን የመንገድ ማስተር ፕላን ሊገናዝቡ እንደሚገባ ቢገለጽም ያላገናዘቡ መሆኑ እና ማስተር ፕላን ላይ ያለውን መንገድ አለማረጋገጥ ችግሮች መኖር፣
- ✓ የመሰረተ ልማት ስራዎች የከተሞችን ማስተር ፕላን/ የከተሞች መሰረተ ልማት ስታንዳርድን (Street standards for Ethiopian urban center, Model urban block standard, Urban greenery standard, etc.) መሰረት ያደረገ አለመሆኑ፣
- ✓ የከተሞች ማስተር ፕላን ሲዘጋጅ መንገድን ብቻ መሠረት ያደረገ መሆኑና ሌሎች የመሠረተ ልማቶችን የሚዘረጉበትን ሥፍራ የማያካትት መሆኑ፣ እንዲሁም ሀገራዊ የመሰረተ ልማቶች የዕድገት አቅጣጫ (National Infrastructure Development Framework) ያለመኖሩ ታውቋል፡፡

92. ኤጀንሲው የተገነቡ ወይም የተዘረጉ የመሰረተ ልማት ስራዎችን የሚያሳዩ ምልክቶችን በቀለም እና ቅርፅ አይነቶች ዲዛይን እና ኮድ ሊያዘጋጅና ተግባራዊ የሚሆኑበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ እንዲሁም የመሰረተ ልማት ስራዎችን የሚያሳዩ ምልክቶቹም በተገቢው ቦታ እንዲደረጉ በማስቻል እና ለሀገራዊ መሰረተ ልማት ቅንጅት የሚሆኑ የተለያዩ የኮድና ስታንዳርድ ስርአቶችና ሰነዶችን በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲደረጉ ሊያደርግ እና አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ✓ የመሰረተ ልማት ስራዎችን የሚያሳዩ ምልክቶች በ2013 ዓ.ም በተዘጋጁት እና በፀደቁት ሁለት ስታዳርዶች ውስጥ የተወሰኑት ቢያዘጋጅም እንዳልተጠናቀቁ፣

- ✓ በአዋጅ 857/2014 አንቀጽ 6(7) መሠረት የሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላትም በምልክቶቹ መሠረት ስለመፈፀማቸው ክትትል ሲደረግ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፤ ኢትዮጵያ ምድር ባቡር፤ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ድርጅት፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ ኢትዮጵያ መብራት አገልግሎት፣ ውሃና ፍሳሽ በተቋማቱ በኩል የመሰረተ ልማት መስመሮች የተቀበሩበትን ቦታዎችን በትክክል ያላመላከቱ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታይተዋል፤

<u>በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ከተሽከርካሪዎች የሚለቀቁ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልኬትና ቁጥጥር ስርዓት አፈፃፀም በተመለከተ</u>

93. ከተሽከርካሪዎች የሚወጡ ሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት መጠንን የሚወስን ስታንዳርድ ሊዘጋጅና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሳቸው በማድረግ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ለማደስ በሚያደርጉት አመታዊ ፍተሻ ወቅት እንደ አስገዳጅ መመዘኛ መስፈርት በማስቀመጥ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

94. በዚሁ መሰረትም በፌደራል ደረጃ የተሽከርካሪ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ለመወሰን በወጣ መመሪያ ቁጥር 35/2011 ከተሽከርካሪዎች ስለሚወጣ ጭስ ልቀት ስታንዳርድ በተመለከተ ለቤንዚን እና ለናፍጣ ተጠቃሚዎች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

    - ✓ ከተሽከርካሪዎች የሚለቀቁ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ያካተተ እና የብክለት ቁጥጥር ማዕቀፍ (frame work) የሌለ መሆኑ፤ እና ከተሽከርካሪዎች ስለሚወጣ ጭስ ልቀት በተመለከተ ስታንዳርድ መሰረት በታህሳስ 2013 ዓ.ም የቀድሞው የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን አስጠንቶ የረቂቅ ስታንዳርዱን ጥናት ለስታንዳርድ ኤጀንሲ መላካቸውን ቢያሳዉቅም፤ አሁን ያለበት ደረጃ መረጃው ለኦዲቱ ያልቀረበ መሆኑ፤
    - ✓ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ለማደስ በሚያደርጉት አመታዊ ፍተሻ ወቅት ወደ አካባቢ አየር የሚለቁት የሙቀት አማቂ ጋዞች መጠን ከስታንዳርድ በላይ እንዳይሆን ለማድረግ የሚያስችል ቴክኒካዊ ፍተሻ እንደ መመዘኛ መስፈርት የማይያዝ መሆኑን፣
    - ✓ አመታዊ ቴክኒክ ምርመራ የሚያከናውኑ ድርጅቶች ያመጡት ውጤት ላይ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልኬት መጠናቸውን ለአሽከርካሪዎች በሚሰጡትና

ለትራንስፖርት ቢሮዎች በኩል በሚልኩት በምርመራ ሪፖርታቸው ላይ የማያመላክቱ መሆኑን ታዉቋል፡፡

95. ከተሽከርካሪዎች የሚለቀቀውን እና የሚቀነሰውን የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን ለመቀነስ ማቀድ እና እየተለቀቀ ያለውን የሙቀት አማቂ ጋዞች መጠንን በትክክል ለመለካት የሚያስችል መሳሪያ ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ ነገር ግን በ2011 እና 2012 በጀት ዓመት ከባቡር ትራንስፖርት ውጭ በሌሎች የየብስ ተሽከርካሪዎች የሚወጡ ሙቀት አማቂ ጋዞችን መጠን ቅነሳ አፈፃፀም አለመኖሩ፤

96. በ2013 በጀት አመት ከየብስ ትራንስፖርት 15.5 ሚሊዮን ቶን ካርበን ለመቀነስ የታቀደ ቢሆንም፤ ስለአፈፃፀሙ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ፤ እንዲሁም በትራንስፖርት ዘርፍ ከአካባቢ አየር ብክለት ጋር በተያያዙ እንቅስቃሴዎችን ለመለካትና ለመገምገም ተገቢ የቴክኒክ ምርመራ መሣሪያዎች እና/ወይም ሌሎች ውጤታማ አማራጭ ቴክኖሎጂዎች አለመኖር፤የድንገተኛ ፍተሻ ለማድረግም ሆነ በአገሪቱ 89 የመንግስትና የግል አመታዊ ቴክኒክ ምርመራ (የቦሎ ምርመራ) ድርጅቶች ውክልና የተሰጣቸው የምርመራ ተቋማቱ የሚጠቀሙባቸው ማሽኖች በትክክል ስለመስራታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ማሽን ወይም የቴክኒክ ባለሙያ አክሪዲቴሽን ተቋም የሌለ መሆኑን ታዉቋል

በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አፈፃፀምን በተመለከተ

97. ባለስልጣኑ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ሥራዎችን በመርሃ-ግብር፣ በስትራቴጂክ ዕቅድ፣ በአመታዊ ዕቅድና በሀገራዊ የልማት እቅዶች ውስጥ እንዲካተት ሊያደረግና አፈፃፀሙን ስለመከታተሉ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ባለስልጣኑ ባወጣው ደንብ ቁጥር 425/2010 መሠረት የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት በሚያስችል መልኩ በመርሃ-ግብር፣ በስትራቴጂክ ዕቅድ፣ በአመታዊ ዕቅድ እንዲሁም በሀገራዊ የልማት እቅዶች ውስጥ ኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻን በተመለከተ በዝርዝር እንዲካተት በማድረግ አፈጻጸሙን ለመለካትና ለመመዘን በሚያስችል መልኩ አቅዶ እየሰራ አለመሆኑ፤

98. በክልሎች የደረቅ ቆሻሻ እና የአደገኛ ቆሻሻ ስራዎችን በዕቅድ የሚተገበር ቢሆንም፣ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ሥራዎችን አስመልክቶ በስትራቴጂክ እና በአመታዊ ዕቅድ ውስጥ አካተው የማይተገብሩና በጋራ አቅደው የማይሰሩ መሆኑ እንዲሁም ይህ እንዲታቀድና እንዲተገበር በባለስልጣኑ የተረገ ድጋፍና ክትትል አለመኖሩ፡፡

99. በተጨማሪም በሀገር አቀፍ ደረጃ የኤሌክትሪክ እና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አመንጪ ከተሞችን ለመለየት እና ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ በጥናት ላይ የተመሠረተ ሥራ ሊሰራ እንዲሁም ጥናቱን ተግባራዊ በማድረግ ያመጣውን ለውጥ ስለመገምገሙ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ባለስልጣኑ በ2013 በጀት ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ የኤሌክትሪክ እና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ጠቋሚ ዕቅድ በማዘጋጀት፣ የዳሰሳ ጥናት የሚደረግባቸውን ክልሎችን በመለየት፣ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል ዕቅድና መረጃ ማሰባሰቢያ ቼክሊስት አዘጋጅቶ ለመተግበር ቢያቅድም በዕቅዱ መሠረት ሀገራዊ ጥናት አለማድረጉ፤

100. የ2013 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሥር የሚተዳደረው አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ በሚገኘው የኮምፒውተር ማወላለቂያ ማዕከል ባለስልጣኑ ባደረገው የመሥክ ምልከታ ማዕከሉ ከተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሰበሰባቸውን በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ ቁሶችን ተረክቦ ያከማቸ መሆኑና ባለስልጣኑም እንዲያስወግዱ ድጋፍና ክትትል ያላደረገ መሆኑ፤

101. በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የአካባቢ ጥበቃ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ቁጥጥር ባለስልጣን በአራት ከተሞች (በዲላ፣ በአርባ ምንጭ፣ በሆሳዕና እና በሶዶ) የሚገኙ 12 የኤሌክሮኒክስ ጥገና በሚሰጡ ተቋማት ላይ በተሰራ የደስሳ ጥናት መሠረት የኤሌክትሮኒክ ቆሻሻዎች በውስጣቸው መርዛማና አደገኛ የሆነ ኬሚካል የያዙ በመሆናቸው ከጥቅም ውጪ የሆኑ የኤሌክትሮኒክ ውጤቶች በአግባቡ የማይያዙና እንደማንኛውም ቆሻሻ የሚያስወገዱ መሆኑ፤

102. የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥራ ላይ ፈቃድ የተሰጣቸው ድርጅቶች የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታዎች የሌለ መሆኑ፤

103. ባለስልጣኑ ለክልል እና ለዞን የአካባቢ ጥበቃ ቢሮዎች በከተሞች የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ በማሰባሰብ፣ በማወላለቅ፣ መልሶ ጥቅም በማዋልና በማስወገድ ስራ ላይ ለመሰማራት ለሚነሳ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሚረዳ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ የድጋፍና የክትትል ስራ እየሰራ አለመሆኑ፤

104. የተራዘመ የአምራቾች ኃላፊነት ስርዓት ባለመዘርጋቱ አምራቾች ለተጠቃሚዎች ከመሸጥ ባለፈ በኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ በወጣው ደንብ መስረት እንዲሰሩ አለማድረጉ፤

105. እያንዳንዱ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻ ዋጋ ያለው ቢሆንም የዕቃው ተፈላጊ አካል ከተለየ በኋላ ጥቅም ላይ የማይውለው የኤሌክትሪክና የኤሌክትሮኒክስ ግንጣይ የሚወገድበት ተገቢ ቦታ የሌለ መሆኑን፣

106. ኢትዮ-ቴሌኮም ከተለያዩ ክልሎችና ዞኖች ከሰበሰባቸው የሚወገዱ ንብረቶች በድምሩ በቁጥር 3,979 (ብር 5 ሚሊዮን አካባቢ ዋጋ ያላቸው) የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ክምችት መኖሩንና ለማስወገድ የተሰራ ስራ አለመኖሩን፣

107. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፋስሊቲዎች አስተዳደር ዋናው መ/ቤት ውስጥ ከተለያዩ ክልሎች እና ዞን ቅርንጫፍ ባንኮች የሰበሰባቸው የሚወገዱ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች በቁጥር 7,798 መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የእንስሳት ብዝሀ ህይወት ሀብት አጠባበቅ እና አጠቃቀም በተመለከተ</u>

108. ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ብዝሀ ህይወት ጥበቃ እና ጥቅም ላይ ማዋልን በተመለከተ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም እንደሀገር የስነ-ምህዳር ግምገማ (Ecosystem Evaluation) የማይደረግ መሆኑ፤

109. የብዝሀ ሕይወት ናሙና ከውጭ አገር ለማስመጣት የሚያችል መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑን፤

110. ከውጪ የእንስሳቱን ዝርያ ወደ ሀገር የሚያስገቡ ተቋማት ወይም የውጪ ድርጅቶች የሚያስገቧቸው የእንስሳት ዝርያዎች በሀገሪቱ ብዝሀ ህይወት ላይ ስለሚያደርሱት

ተፅእኖ ምንም አይነት ውል እና ስምምነት ሳይኖር የሚያስገቡና የሚሰሩ መሆኑ፣ እንዲሁም በሀገሪቱ ብዝሀ ህይወት ላይ የሚያደርሱት ተፅእኖ ያልተጠና መሆኑን፤

111. የብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ተመሳሳይ ስራዎች ለተለያዩ የመንግስት ተቋማት (በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ በግብርና ሚኒስቴር እና በንግድ ሚኒስቴር) በመሰጠቱ እና የተግባርና ሀላፊነት መደራረብ ምክንያት የሀብት እና የጊዜ ብክነት መፈጠሩና ችግሩን ለመፍታት ኃላፊነት ተወስዶ ያልተሰራ መሆኑ፤

112. የግብርና ሚኒስቴር እንሰሳት ለንግድ ከውጭ ለማስገባት ይሁን ለማስወጣት የቬተርነሪ ሰርተፊኬት የሚሰጥ ሲሆን፤ በዚህ ፈቃድ መሰረት ወደ ሀገር የሚገቡት እንሰሳት በስነ ምህዳሩ ላይ ሊያርደስ ስለሚችለው ጉዳት ጥናት ሳይደረግ ወደሀገር የሚገቡ መሆኑ፤ ለአብነት ያህል በቡታጅራ ከተማ የወጭ ዜጎች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ወስደው ቬተርነሪ ሰርተፊኬት ስላገኙ ብቻ የአይጦችን ዝርያ ከውጪ በማስገባት እያረቡ ለምርምር የሚጠቀሙበት ሁኔታ ያለ መሆኑን እና የአይጥ ዝርያዎቹም አገልግሎታቸውን ሲጨርሱ የሚቃጠሉ እና የሚጣል መሆኑ ይህም በአካባቢው ብዝሀ ህይወት ላይ የሚያደርሱት አሉታዊ ተፅእኖ ሊያስከትለዉ የሚችለዉ ችግር ያልተጠና (ያልታወቀ) መሆኑን፣

113. ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ጀነቲክ ሀብት ዝውውርን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ ያላዘጋጀ እና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣ የጀነቲክ ሀብት አርክቦት እና ጥቅም ተጋሪነት ክትትልን በተመለከተ የቁጥጥር ቦታዎች (ኬላዎች) ላይ ያልተሰራ መሆኑን፤

114. በኢንቨስትመንት የሚሰጡ ፍቃዶች አማካኝነት ህገ-ወጥ የጀነቲክ ሀብት ዝውውር መኖሩን፤ ወራሪ መጤ ዝርያን ለመቆጣጠር ጢንዝዛን ወደ ሀገር የሚያስገቡ ተቋማት ህግን የተከተሉ ስለመሆኑ ክትትል የማይደረግ መሆኑን፣ በሕጉ መሰረት የአርክቦት ውሎችን ተደራድሮ መዋዋል፣ የአርክቦት ፈቃድ መስጠት እና ተግባራዊነታቸውን መከታተል በተመለከተ የክትትል ስራው ተጠናክሮ ያልተሰራ መሆኑን፤ በኬላዎች ላይ ብዝሀ ህይወትን በተመለከተ የቁጥጥር ስራውን የሚሰራ ባለሙያ የሌለ መሆኑን፣ አንዳንድ ተማሪዎች የንብ ናሙናን ይዘው ወደ ውጪ የሚወጡ መሆኑን እና ንብ ዝርያ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር የላላ መሆኑን እንዲሁም

ለማር የሚያገለግሉ የንብ ዝርያዎች በውጪ ዜጎች ያለፍቃድ የሚወሰዱበት ሁኔታ ያለ መሆኑን፣ የአሳ ዝርያ ላይ ጀነቲክ ቁጥጥር የሌለ መሆኑን፣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራዝ የመንገድ አስተዳደር ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ

115. በክፍያ መንገዱ ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን ለመቀነስ ከክብደት በላይ ጭነው የሚመጡ ተሽከርካሪዎችን የክፍያ መንገድ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ በመሆኑ ይህንን ጉዳት ለመቀነስ የክብደት መለኪያ ሚዛን በመግቢያ በሮች ላይ በመትከል በመንገድ ደህንነት አስተዳደር በውስጥ አሰራር ማኑዋሉ መሰረት መቆጣጠር ሲገባው፣ በድሬደዋ ደወሌ ክፍያ መንገድ ከክብደት በላይ ጭነው ወደ ክፍያ መንገዱ የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን ለማስቆም ግልፅ መመሪያ ባለመኖሩ ከክብደት በላይ ጭነው ወደ መንገዱ በሚገቡ ተሽከርካሪዎች ላይ በተደረገ ቁጥጥር በ2012 በጀት ዓመት በሁለቱ ቋሚ የክብደት ሚዛን ቁጥጥር በማድረግ 34,440 ተሽከርካሪዎችን መመዘን የተቻለ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 13,776 ተሽከርካሪ (40 በመቶ) ከተፈቀደ ክብደት በላይ የጫኑ ሲሆን በ2013 በጀት ዓመት በላስድሬ ክፍያ ጣቢያ በ18,012 ተሽከርካሪዎች ላይ በተደረገ ፍተሸ 2,194 (12 በመቶ) እንዲሁም በቢየድሌ ክፍያ ጣቢያ በ5,811 ተሽከርካሪዎች ላይ በተደረገ ፍተሻ 746 (13 በመቶ) ከክብደት በላይ ጭነው መንገዱን የተጠቀሙ በመሆኑና መንገዱን እንዳይጠቀሙ ለማድረግ ባለመቻሉ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ የሚገኝ መሆኑን፣

116. በድሬዳዋ ደወሌ የክፍያ መንገድ ላይ ከክብደት በላይ ጭነው ወደ መንገዱ ውስጥ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች በመንገዱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ መሆኑን ተከትሎ ከክብደት በላይ በጫኑ ተሽከርካሪዎች ምክንያት በመንገዱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የስራ ተቋራጩ (CGC Overseas construction group CO,LTD) ጥገና እንደማያከናዉን ያሳወቀ ሲሆን ይህን ችግር ለመቅረፍም በኢንተርራይዙ እና በሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካለት የጋራ መፍተሄ ያልተቀመጠ መሆኑ

117. በኢንተርፕራይዙ ክፍያ መንገድ ላይ ከተፈቀደው ፍጥነት በላይ በማሽከርከር የሚደርሰውን አደጋ ለመቀነስ እና በክፍያ መንገዱ ላይ የተቀመጡ ህጎችና ደንቦችን ጠብቆ በማሽከርከር የመንገድ ፍሰቱ በማቀላጠፍ የትራፊክ ደህንነቱ የተጠበቀ

እንዲሆን እና ዘመናዊ የመንገድ ደህንነት ቴክኖሎጂዎችን እና ምልክቶችን በመጠቀም የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስ ዘመናዊ የፍጥነት ቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት ሊሰራ እንደሚገባ በኢንተርፕራይዙ ስትራቴጂክ እቅድ የተገለጸ ቢሆንም፡- በአዲስ አዳማ ፍጥነት መንገድ እና በድሬደዋ ደወሌ ከፍያ መንገድ ላይ የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች በተፈቀደላቸው የፍጥነት ወሰን መሰረት እንዲጓዙ የሚያስገድድ ህግ የተቀመጠ ቢሆንም ይህንን ለማስፈጸም የሚረዱ ዘመናዊ የፍጥነት ቁጥጥር ስርዓት ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን፤

118. በአዲስ አዳማ ፍጥነት መንገድ ላይ የአደጋ መንስኤዎች ከሆኑት አብዛኛውን ፍጥነት መሆኑ በጥናት የተረጋገጠ ቢሆንም ይህንን ለመቆጣጠር ራዳር (የፍጥነት መቆጣጠሪያ መሳሪያ)፣ የመገናኛ ራዲዮ እና የአልኮል ልኬት መመርመሪያ መሳሪያ ለመግዛት ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ጥያቄ ቢቀርብም ሊፈጸም እንዳልተቻለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን የቅመማ ቅመም ልማትና ግብይት ስርዓት አፈፃፀም በተመለከተ

119. ባለስልጣን መ/ቤቱ ዘመናዊ የቅመማ ቅመም ሰብሎች ልማትና ግብይት ለማጠናከርና ለማስፋፋት የሚረዳ የህግ ማዕቀፍ ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ መመሪያዎችን አውጥቶ መተግበር ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም፤የቅመማ ቅመም ምርቶች ዘመናዊ ግብይት ማስፈጸሚያ የህግ ማዕቀፍ (አዋጅ ወይም ደንብ) ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፣ የቅመማ ቅመም ግብይትና ጥራት ቁጥጥር መመሪያ በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት የተደረገበት እና ለግብርና ሚኒስቴር የተላከ ቢሆንም እስከ ታህሳስ 30/2014 ያልፀደቀ መሆኑ፤

120. ባለስልጣኑ የቅመማ ቅመም ምርት ጥራት፣ በህግ ሃላፊነት ከተሰጣቸው አካላት ጋር በመተባበር የብሔራዊ የጥራት ደረጃ እንዲያወጣ እና የቅመማ ቅመም ምርት ጥራትና ጣዕም ምርምር ማዕከላት ሊያቋቁም የሚገባ ቢሆንም፡- የቅመማ ቅመም ምርት የጥራት ደረጃ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣ በህግ ሃላፊነት ከተሰጣቸው አካላት ጋር በመተባበር የቅመማ ቅመም ምርት ብሔራዊ የጥራት ደረጃ ያልተወሰነ መሆኑና፣ የቅመማ ቅመም ምርት ጥራትና ጣዕም ምርምራ ማዕከላት ያልተቋቋሙ መሆኑ፤

121. ባለስልጣኑ ለቅመማ ቅመም ምርቶች ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ሊዘረጋና አፈፃፀሙን ሊከታተል፣ ለዚህም የሚያግዙ የግብይት ማዕከላትን በክልሎች ሊያቋቁምና ተቋማቱ ዘመናዊ የግብይት አሰራር ለግብይት ተዋንያን ተገቢውን አገልግሎት መስጠታቸውን ሊደግፍና ሊከታተል ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡-ለቅመማ ቅመም ምርት ዘመናዊ የግብይት ስርዓት የውጭ ንግድ ኮንትራክት ምዝገባንና ክትትል ጨምሮ) ያልተዘረጋ መሆኑ፤ በሀገሪቱ የሚካሄደው የቅመማ ቅመም ግብይት ሰንሰለት ረጅም መሆኑ፤ ለጥራት ጉድለትና ለህገ-ወጥ ንግድ በር የሚከፍት እንዲሁም አርሶ አደሩን ቀጥተኛ ተጠቃሚ የማያደርግ መሆኑ፤ ለቅመማ ቅመም አምራቾች፣ አቀነባባሪዎች እና ላኪዎች በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ቀጥታ ለመሸጥ ምቹ የሆኑ የግብይት ማዕከላት አለመቋቋማቸው ታውቋል፣

122. ባለስልጣኑ በቅመማ ቅመም ምርቶች ላይ እሴት ለመጨመር የሚያስችል ሀገራዊ አቅም እንዲገነባ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሊሰራ እና እሴት የተጨመረባቸውን ምርቶች ወደ ዓለም ገበያ ለማስገባት የሚያስችል ስልት ነድፎ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

123. ነገር ግን በቅመማ ቅመም ምርቶች እሴት መጨመርን በተመለከተ በዝርዝር እቅድ ውስጥ ያልተያዘና ያልተሰራ መሆኑ፣ በናሙና በታዩ አካላት በቅመማ ቅመም ምርቶች ላይ እሴት ለመጨመር የሚያስችል ሀገራዊ አቅም እንዲገነባ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የተሰራ ስራ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

<u>የአዳሚ ቱሉ ፀረ-ተባይ ፋብሪካ የሥራ አፈጻጸም ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ</u>

124. ፋብሪካው ግዥዎችን ሲፈጽም ጥቅም ላይ የሚያውላቸው፤ የሚያሰራጫቸው ለአገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች፣ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ከአቅራቢዎች ከመገዛታቸው በፊት አካባቢን የማይበክሉ ስለመሆናቸው ሊያረጋግጥ እንደሚገባና ተጠሪ መስሪያ ቤት የሆነው የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዢ መመሪያ ቁጥር 07/2012 ገፅ 11፣ በሥሩ ያሉ ፋብሪካዎች ለምርት አገልግሎት የሚውሉ

ግዥዎችን ሲፈጽም በዕቅድ ሊመራና በተፈለገው ጊዜ፣ መጠን፣ ጥራት እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ሊሆን እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡

125. በዚሁ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፋብሪካው ግዢ ፈጽሞ ጥቅም ላይ የሚያውላቸው፤ የሚያሰራጫቸው ለአገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች፣ ምርቶች ከአቅራቢዎች ከመገዛታቸው በፊት አካባቢን የማይበክሉ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣ በተጨማሪም መመሪያቸዉ ላይ ፋብሪካው ገዝተው የሚጠቀማቸው፤ የሚያሰራጫቸውና ለአገልግሎት የሚውሉ እቃዎችና ምርቶች በአካባቢ ላይ ብክለትና የተለያዩ ተፅዕኖዎችን የማያሳድሩ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ እንደሚገባ ቢደነግግም አካባቢ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ በፋብሪካው የአካባቢ ጥበቃ ሥርዓት በመዘርጋት በዕቅዱ ውስጥ አካቶ ያልሰራና፣ በአካባቢ ላይ ተፅፀኖ ሊያሳድሩ የሚችሉትን መለየት ያልቻለ እና በፋብሪካው የአካባቢ ተፅፅኖ ግምገማ ያላደረገ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ የሌለው መሆኑንና ፋብሪካው ገዝቶ የሚጠቀማቸው ኬሚካሎችና ምርቶቹ በአካባቢው ላይ የሚያደርሱትን ብክለት ያላረጋገጠ መሆኑን በኦዲቱ ታይትዋል

የአዋሽ ተፋሰስ ልማት ጽ/ቤት የተፋሰስ ልማትና
የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥራ አፈጻጸም በተመለከተ

126. በተፋሰሶች ልማት ባለስልጣን ለአዋሽ ተፋሰስ ልማት ጽ/ቤት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 441/2011 በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሠረት በተፋሰሱ ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደትን ለማስፈፀም የሚረዱ ተግባራትን ለማከናወን የውሃ አጠቃቀምን በፍቃድ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት ብሎ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን በተፋሰሱ የውሃ ሀብት ልማትና ብዝሀ ህይወትን ለማስተዳደር የሚረዳ የተፋሰስ እንክብካቤ እና ልማት የአፈጻጸም መመሪያ /Guideline/ ያላዘጋጀና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

127. የተፋሰሱን የውሃ አጠቃቀም ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል የቁጥጥር መመሪያ የሌለ በመሆኑ፣ የወንዝ አመራር ስራ ለመስራት የሚያስችል የአሰራር መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣ ጽ/ቤቱ የተፋሰሱን የውሃ ሀብት አስተዳደር በተቀናጀና አሳታፊ በሆነ የአጠቃቀም ስርዓት በተፋሰስ ዕቅድ መሰረት ያላከናወነ መሆኑ፣ጽ/ቤቱ የውሃ ሀብትን ከማልማትና ከማስተዳደር አንፃር የውሃ ሀብትና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን፣ በማደራጀትና ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች

እንዲውል ለማስቻል የውሃ ሀብት የማስተዳደር ሥራዎች በተገቢው መንገድ ያልተሰሩ መሆኑ፤

128. ጽ/ቤቱ በአዋሽ ተፋሰስ ውስጥ የተፋሰሱን የውሃ ሀብት ግኝት በመጠን በጥራት በቦታና በጊዜ ሊለይ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ የተፋሰሱን የውሃ ሀብት ግኝት በመጠን በጥራት በቦታና በጊዜ ያልተለየ መሆኑ፣ ጽ/ቤቱ በላይኛው፣ በመካከለኛውና በታችኛው አዋሽ ተፋሰስ ያሉ የውሃ ተጠቃሚዎችን መረጃ በመሰብሰብ፣ የውሃ አጠቃቀምና የታከመ ፍሳሽ ልቀትን ወደ ፍቃድ ስርዓት አለማስገባት ያሉትን የውሀ ምንጮችን መጠን እና ጥራት ደረጃ በመለየት ለዘላቂ የውሃ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም ሂደት ስራዎችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ያልሰራና አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፤

129. የወንዝ አመራር ዋና ዓለማ በጥናት ላይ የተመሰረቱ የወንዝ አመራር ስራዎችን በማቀድ፤ በመተግበርና በማስተግበር የውሃ እጥረትን መቆጣጠር እና በተለያዩ አካባቢያዊና ሰው ሰራሽ ተጽእኖዎች ምክንያት የሚከሰት የጎርፍ አደጋን በመከላከል የተፋሰሱ ማህበረሰብ የላቀ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እና ተፋሰሱ ስነምህዳሩን የጠበቀና ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ቀጣይነት ያለው አስተዋጽኦ እንዲኖረው ማስቻልና ተፋሰሱን ተክትሎ ሊከሰቱ የሚችሉ የጎርፍ ስጋቶችን በጥናቶች ላይ በመመስረት ደረጃቸውን የጠበቁ የጎርፍ መከላከያ ዳይኮች (ዱካዎች) መሠራታቸውን ማረጋገጥ ይኖሪበታል፡፡

130. ይሁን እንጂ በዚህ መሰረት ስለመከናወኑ ኦዲት ሲደረረግ፤ የአዋሽ ተፋሰስ ከመልክዓ ምድራዊ አቀማመጡ ጋር ተያይዞ ከመካከለኛ እስከ እጅግ በጣም ከፍተኛ ደረጃ ለጎርፍ ተጋላጭ አካባቢዎች እንደሚገኙበት የተለያዩ ጥናቶች የሚያሳዩ ሲሆን፤ ከአጠቃላዩ የተፋሰሱ ስፋት 114,123 ስኩዌር ኪሎ ሜትር መካከል 84.4% የሚሆነው ከመካከለኛ እስከ በጣም ከፍተኛ ለጎርፍ ተጋላጭ ነው፡፡ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰፊውን የተጋላጭነት ድርሻ የሚይዝ መሆኑና የተጋላጭነት ደረጃውም እጅግ በጣም ከፍተኛ ደረጃ የሚደርሱ ከክልሉ ወረዳዎች መካከል አሚባራ፣ ዱለቻ፣ ገዋኔ፣ ገለዓሎ፣ ዱብቲ፣ አሳይታና አፋምቦ ወረዳዎች የሚገኙ ቢሆኑም ጽ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የሠራቸው ስራዎች አጥጋቢ አለመሆናቸው እና ችግሩ ኦዲቱ እስከ

ተከናወነበት ጊዜ የቀጠለ መሆኑ፤ ለማሳያ ያህልም **በአፋር ክልል አሚባራ ወረዳ አባቢ በክረምት በነበረው የጎርፍ አደጋ 8,724.74 ሄክታር የእርሻ መሬት በውሃ በመሸፈኑ መሰረተ ልማቶች ከጥቅም ውጭ መሆናቸው፣**

131. በ2012 ዓ.ም የአዋሽ ወንዝ በገለዓሎ ወረዳ ላይ ሁለት ቦታዎች እንዲሁም ገዋኔ ወረዳ ላይ ሁለት ቦታዎች በመስበር ከ600 ሄክታር በላይ የሽንኩርት፤ የጥጥ፤ሰሊጥ የደረሰ የእርሻ ልማት ያጠፋ መሆኑ፣በኦዲቱ ታይቷል፡፡

132. የጎርፍ ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሞዴሎች ጥናት በአዋሽ ተፋሰስ ውስጥ /flood vulnerability digital map preparation/ በ2009 እስከ 2011 ዓ.ም ብር 36,906,160.30 ለጥናት ወጭ የተደረገ ቢሆንም፤ እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ በጥናቱ መሰረት ወደትግበራ ያልገባ መሆኑ በኦዲቱ ታይትዋል

<u>በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የስራ ምዘናና ደረጃ አወሣሰን ፕሮጀክት ጄ/ኢ/ጂ አፈጻጸም ውጤታማነትን በተመለከተ</u>

133. ኮሚሽኑ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ከሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም አንዱ የሆነውን የሰው ኃይል ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በኮሚሽኑ መሪነት እየተገበረ ሲሆን፤ ሙሉ ለሙሉ የተተገበረው ግን በ2011 ዓ.ም ነዉ፤ ይህም ጥናቱ ታሳቢ የሚያደረጋቸው መስፈርቶች በ 20 አመታት ውስጥ ተለዋዋጭነት ሊኖራቸው ስለሚችል ወቅታዊነት እና ውጤታማነቱን ሊቀንሰዉ የሚችል መሆኑ፤

134. በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ ብዛታቸዉ 18,000 በላይ የሆኑ የሥራ መደቦችን ምዘና አካሂዶ ባስመዘገቡት አጠቃላይ ነጥብ መሰረት በ 22 የሥራ ደረጃዎች /Grade/ እንዲገቡ ያደረገ ሲሆን የመደቦቹን አስፈላጊነት እና የስራ መደቡን የስራ ጫና በመዋቅር እና በአደረጃጀት ለማስተካከል እድል ያልሰጠ መሆኑ፤

135. ሥራዎቹን ቀደም ብሎ ከተተገበሩት የማኔጅመንት መሳሪያዎች (ቢ.ፒ.አር፣ ቢ.ኤስ.ሲ፣ ኤ.ቢ.ኤም እና ከመሳሰሉት) የተሻለ አገልግሎትን በሚያቀላጥፍ፣ እና ወጪን ሊቆጥብ የሚያስችል አሰራር እንዲዘረጋ አለማስቻሉ፤

136. በፌደራል መንግሥት ሰራተኞች አዋጅ 1064/2010 አንቀጽ 22 መሰረት ሥራዎችን በውል ለሶስተኛ ወገኖች አሸጋግሮ ማሰራት እንዲሁም አንቀጽ 23

የመንግስት ሰራተኞችን በጋራ ስለመቅጠር የተቀመጡ አማራጮችን ለመጠቀም መዋቅራዊ እድል ያልሰጠ መሆኑ፤

137. የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ያለው ከፍተኛ የሰው ኃይል ቁጥር (ሁለት ሚሊዮን አካባቢ) አስተዳደራዊ ለውጦችን ለማድረግ አዳጋች በመሆኑ ይህም በሀገር አቀፍ ደረጃ በጄኢጄው ምክንያት በተደረገ የደመወዝ ለውጥ ምክንያት 32 ቢሊዩን ብር ዓመታዊ ጭማሬ ቢያስከትልም፤ ዝቅተኛው መነሻ የሲቪል ሰርቪስ ደሞዝ አሁንም ዝቅተኛ መሆኑ/ይህም ኮሚሽኑ የሥራ ምዘና እና ደረጃ አወሳሰን ፕሮጀክት ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት ፋይናንሻል አዋጭነቱን እንዲሁም የሲቪል ሰርቪሱን ሙሉ አቅም ለመጠቀም እና አገልግሎትን በይበልጥ ለማሳደግ የሚያስችሉ መዋቅሮች የሚመለከቱ ጥናቶች በማጥናት መዋቅራዊ አደረጃጀቱን ማስተካከል አለመቻሉ፤

138. በሰው ኃይል አስተዳደር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ስር የተነደፉ ሌሎች 4ቱ (የሥራ አፈጻጸም ምዘናና የጊዜ አጠቃቀም ፕሮጀክት፣ የክፍያ ስርዓትና የሥራ ሁኔታዎች ፕሮጀክት እና የሰው ኃይል ብቃት ፕሮጀክት፣ የሰው ኃይል እቅድ ፕሮጀክት፣) ተግባራዊ ባለመሆናቸው ምክንያት በጄኢጄው ውጤታማነት ላይ ተጽእኖ ማሳደራቸው፤

<u>**በጅማ ዩኒቨርሲቲ የግብርና ዘርፍ ምርምር አፈጻጸም እና የዩኒቨርስቲው የምርምር ፈንድ አስተዳደር ስርዓት ኢኮሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆናቸውን በተመለከተ**</u>

139. በጅማ ዩኒቨርሲቲ የግብርና እና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ የሚከናወኑ የግብርና ዘርፍ ምርመር ሥራዎች አዳዲስ እውቀትና ቴክኖሎጂን በማፍለቅ፣ በማሰራጨት የህብረተሰቡን ጥያቄ ምላሽ በመስጠት ላይ ሊያተኩር ይገባል፡፡

140. ነገር ግን በግብርና እና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ የሚካሄዱ የምርምር ስራዎች በአብዛኛው በዳሰሳ ጥናት ላይ ብቻ ያተኮሩ መሆኑ፤

141. የግብርና ዘርፍ የምርምር ሥራዎች አፈፃፀም አናሳ መሆናቸው፣ በተለይም ምርምሮች የህብረተሰቡን ችግር ለመቅረፍ ከፍተኛ ጥራት፤ ተገቢነት ባለው እና በሚጠበቀው ደረጃ ላይ የማይገኙ መሆኑ፤ ለምሳሌ የማህበረሰቡን አንገብጋቢ ችግር

ሊፈቱ የሚችሉ ዝርያ ማውጣት/ ማላመድ ስራ በብዛት ያልተሰራ መሆኑ እና አብዛኛዎቹ የምርምር ላቦራቶሪዎች ከመማር ማስተማር በተጨማሪ የምርምሩን ስራ እየደገፉ አለመሆኑ፤

142. ዩኒቨርሲቲው የግብርና ዘርፍ የምርምር ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ለማድረስ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ላይ ይገኛል ቢባልም፣ ለተጠቃሚው የሚደርስበት መንገድ ያልተጠቀሰ እና ምን ያህል የምርምር ውጤቶች ለተጠቃሚዎች እንደተሰራጩ የማይታወቅ መሆኑ፣

143. አብዛኞቹ ላቦራቶሪዎች ለመማር ማስተማር ብቻ እንጂ የህብረተሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ የግብርና ዘርፍ የምርምር ስራዎች የማይሰሩ መሆኑ፤

144. ዩኒቨርሲቲው ለጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚያግዙ መሰረተ ልማቶች (የምርምር ማዕከላትን፣የስልጠና ማዕከላት እና ላቦራቶሪ ወዘተ…) ሊያቋቁም እና አቅማቸውን የማጎልበት ስራ ሊሰራ –የሚገባ ቢሆንም፡-

145. በ2002 ዓ.ም ጨረታ ወጥቶ በ13 ወር ለመጠናቀቅ የተጀመረው የእንስሳት ህክምና የምርምር ማዕከል፣ ላብራቶሪ ስራው ሳይጠናቀቅ 12 ዓመት የፈጀና አሁንም ያልተጠናቀቀ መሆኑ፤

146. ዩኒቨርሲቲው በግብርና ዘርፍ የሚካሄዱ ምርምሮች ለሴቶች እና ወጣት ተመራማሪዎች የፈጠራ ምርምር ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ እና አዲስ ምርት፤ አገልግሎትና ቴክኖሎጂን ለማፍለቅ የጥናትና ምርምር ቦታዎችን በመለየት እና በማመቻቸት ልዩ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

147. ነገር ግን በወጣትና ሴቶች እስካሁን የተከናወኑ ምርምሮች 2012 ዓ.ም በመሪ ተመራማሪነት 175 ሴት መምህራን ለማሳተፍ አቅዶ 43 ሴት መምህራን ብቻ እንዲሳተፉ ያደረገ መሆኑ፤ ይህም አፈጻፀሙ 25 ከመቶ ብቻ የተከናወነ መሆኑ ከአጠቃላይ ምርምሮች ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ መሆኑ፤

በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ማምረቻ ኢንዱስትሪ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ

148. ኢንዱስትሪው ተሽከርካሪዎችን ለማምረትና ለመገጣጠም የሚውሉ እቃዎች /ግብዓቶች/ ግዥ፤ የግዥ ፍላጎትና መመሪያን ተከትለው የተፈፀሙ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

149. ነገር ግን በቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ በስሩ ለሚገኙ አምስት ፋብሪካዎች እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚገኘው በሴንትራል ሪፈራል ጋራዥ የኢንዱስትሪው የግዥ ስርዓት ህግና አሰራርን ያልተከተለ፣ ቀልጣፋና ወጭ ቆጣቢ አለመሆኑና ለስራ መጓተትና ለሰራተኛ ሮሮ የተጋለጠ መሆኑ፣

150. ኢንዱስትሪው በቀድሞው ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን በአሁኑ የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ በኩል ከ2002 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም ባለው ጊዜ ያለ ምንም የውጭ አገርና የአገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ፣ ያለ ግዥ ፍላጎትና እቅድ፣ አስቀድሞ በጀት መያዙንና በማን በኩል እንደተጠየቀ ሰነድ ባልተገኘበት እንዲሁም የደንበኞችን ፍላጎት ማዕከል ባላደረገ መልኩ ግዥ መፈፀሙ፣

151. ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ሀምሌ 01/2003 ዓ.ም እና ህዳር 01/2012 ዓ.ም ተሸሽሎ የወጣውን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ፣ እንደ ግዥው ባህሪና የዋጋ መጠን ላይ ተንተርሶ እንደ አስፈላጊነቱ በአገር አቀፍና አለም አቀፍ ጨረታ አወዳድሮ ግዥ ማከናወን እንደሚገባ በመመሪያው ላይ በግልፅ ቢቀመጥም ያለ አግባብ በአጠቃላይ የውል ዋጋ 952,561,000.00 USD እና 27,889,913.50 EURO የውል ስምምነት የተከናወነበትና ኢንዱስትሪው ለውል ተቀባይ ብር 2,473,083,389.59 የገንዘብ መጠን የተከፈለ መሆኑ፣

152. ኢንዱስትሪው የምርት ሽያጭ ገቢውን ወቅቱን ጠብቆ የሚሰበስብበትና በየጊዜው ሪፖርት የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ለ73 ተቋማትና እህት ኢንዱስትሪዎች ብር 1,714,207,081.32 በዱቤ ሽጦ ገንዘቡ ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

153. ኢንዱስትሪው የሚከፍላቸው አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች ደንብ እና መመሪያን መሰረት ማድረግ የሚጠበቅባቸዉ ቢሆንም፣ ኢንዱስትሪው ከተቋቋመበት አላማ ውጪ ገንዘብ የማበደር የህግ መብት ሳይኖረው ለድጋፍ በሚል ለንጋት ኮከብ ትራንስፖርት አገልግሎት አክስዮን ማህበር በባንክ ወጪ ሰነድ ቁጥር 6007 ብር 18,000,000.00 /አስራ ስምንት ሚሊዮን/ ብድር የሰጠ መሆኑና ብድሩ ለተቋሙ ተመላሽ አለመደረጉ እንዲሁም ኢንዱስትሪው ከባንክ ወለድ ሊያገኝ የነበረውን 3,240,000.00 ብር እንዲያጣ ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፣ በተጨማሪም በኢንዱስትሪው በ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት በወቅቱ የነበሩ ኃላፊዎች በቁጥር 25 ዳብል ጋቢና ፒክ አፕ መኪኖችን በደብዳቤ የወሰዱ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ከደብዳቤ ወደ ውለታ ተቀይሮ ክፍያ መጠየቅ አለመቻሉ፣ በኦዲቱ ታይቷል፡፡

<u>ልዩ ኦዲት</u>

154. መ/ቤታችን በዕቅድ ከያዝናቸዉ የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በተለያዩ አካላት በርካታ የልዩ ኦዲት ጥያቄዎች ቀርበው በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን በተወሰኑ ቅድሚያ ከተሰጣቸው 11 ልዩ ኦዲቶች ሥራቸው ተጠናቆ ሪፖርታቸው ለሚመለከታው አካል ተልኳል፡፡ 8 ልዩ ኦዲቶች ኦዲታቸዉ በመሰራት ላይ ሲሆን ሲጠናቀቁ ለጠያቂዉ አካል የሚላኩ ይሆናል፡፡

<u>በመ/ቤታችን በተሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ</u>

155. በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡

156. በዚሁ መሰረትም በ2012 በጀት ዓመት እና ቀደም ባሉት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ100 መ/ቤቶች እና በ27 ቅ/ጽ/ቤቶች

በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተመላሽ እንዲደረግ ተብሎ አስተያየት ከተሰጠበት ሒሳብ ብር 2,471,480,929.1 እና 492.328 የአሜሪካ ዶላር እንዲሁም 222.68 ዩሮ ውስጥ ብር 1,442,314,002.02 እና 492.328 የአሜሪካ ዶላር እንዲሁም 222.68 ዩሮ እርምጃ ያልተወሰደበት ቀሪ ሂሳብ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ብር 1,029,166,927.12 ተመላሽ መደረጉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

157. በተጨማሪም በገቢ አሰባበሰብ ዙሪያ እስከ 2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ ላይ እርምጃ ሳይወሰድባቸው በቀሪነት የሚታይ፤ በገቢዎች ሚኒስቴር 11 ቅ/ጽ/ቤቶች እና በጉምሩክ ኮሚሽን 8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 331,700,959.3 እርምጃ እንዳልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

158. ይህ አፈጻጸም ተመላሽ ሊደረግ ከሚገበው ሂሳብ ጋር ሲነፃፀር በመቶኛ 41.64% ሲሆን፤ ቀሪው ብር 1,442,314,002.02 እና 492.328 የአሜሪካ ዶላር እንዲሁም 222.68 ዩሮ ተመላሽ ያልተደረገ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህ አፈፃፀም ከነበሩት ዓመታት የተሸለ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

159. ቢሆንም መሥሪያ ቤቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰዱ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፤ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ፤ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

160. በዚህ አጋጣሚ የገንዘብ ሚኒስቴር የፋይናንስ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ባልተወጡ የተቋማት የስራ ሃላፊዎች ላይ የወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ተገቢነት ያለውና ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ተግባር በመሆኑ መ/ቤታችን ሚኒስቴር መ/ቤቱን እያመሰገነ ወደፊትም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል እንላለን፡፡

የተከበሩ አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የመ/ቤታችን ዋና ዋና የድጋፍ ዘርፍ አፈጻጸምን በሚመለከት

የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ

161. መ/ቤታችን የዉጤት ተኮር ሥርዓት ግንባታ ተከትሎ ለእያንዳንዱ ሰራተኛ ስራን ቆጥሮ በመስጠት ሥራዎቹ እስከ ሠራተኛ ድረስ በማውረድ ካስኬድ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት ስራዎቹ እየተከናወኑ ሲሆን የስራ አፈጻጸም ምዘናም ወቅቱን ጠብቆ በመሞላት ላይ ነዉ፡፡ አገልግሎት አሰጣጣችን ይበልጥ ተደራሽ እንዲሆን የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ፕሮቶኮል በሚል በማሳተም ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች እየተሰራጨ ይገኛል፡፡

162. ከሀምሌ 2013 እስከ መጋቢት/2014 በ9 ወራት ውስጥ የተለያዩ አገልግሎት ለማግኘት ወደ መ/ቤታችን የመጡ 1,265 ተገልጋዮች ሁሉም ተገልጋዮች በአግባቡ ከመ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ተደርገዋል፡፡

163. የመ/ቤቱ ሁሉም ሠራተኞች ሃብታቸውን ያስመዘገቡ ሲሆን የተመዘገበውን መረጃ በማደራጀትና ወቅታዊ በማድረግ ለስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተልኳል፡፡ ከዚህም ሌላ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ዲጅታል በመሆኑ የሁሉንም ሰራተኞች ንብረት በአዲስ መልክ ለመመዝገብ ቅድመ ሁኔታዎች እየተመቻቹ ይገኛል፡፡ በአለም አቀፍ የኦዲት ስታንዳርድ መሰረት ኦዲተሮች የስራ ስብጥር ወይም የሪሻፍሊንግ ስራ ተከናውኗል፡፡

164. በመ/ቤቱ የጥቆማ መቀበያ ሳጥን፣ የውስጥና የውጭ ስልክ፣ የኢሜል አድራሻ በማሳወቅ ስርዓት ተዘርግቶ ጥቆማ ያላቸው አካላት የተዘረጋውን ስርዓት በመጠቀም ጥቆማ እንዲያቀርቡ ሁኔታዎች ተመቻችቷል፡፡ ለሁሉም አመራርና ሰራተኞች

በመልካም ስነ-ምግባርና ግንባታ ሞራል እሴቶች ግንባታ ላይ እና ሙስና መከላከል ላይ በጸረ ሙስና ባለስልጣን ባለሙያዎች አማካኝነት የካቲት 18/2014 ዓ.ም ለ472 ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ

165. በፋይናንስ እና ህጋዊነት እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቶች ለሴቶች፤ ወጣቶች፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋውያን ወዘተ በህግ የተጠበቁ መብቶች ተጠቃሚነትና የአገልግሎት ተደራሽነት በተመለከተ ሁሉም የሥራ ክፍሎች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን የዕቅዳቸው አካል አድርገው እንዲያቅዱና በኦዲቱ ትኩረት ሰጥተዉ እንዲያዩት ተደርገዋል፡፡

166. በሌላ በኩል በዚህም ዓመት ዓለም አቀፍ የሴቶችና የፀረ-ጾታ ጥቃት፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ወጣቶችና የህፃናት ቀን መደገፍ እንደዚሁም የኤች አይ. ቪ. ኤድስ ቀናት በተለያዩ ትምህርታዊና የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ታጅበው በመ/ቤቱ ተከብሯል፡፡ በተጨማሪም በየ 2 ወሩ በመደበኛነት የሚካሄደው የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች የልምድ መለዋወጫ መድረክ አሁንም ቀጥሎ በመካሄድ ላይ የሚገኝኝ ሲሆን፣ 70 ሴት ሠራተኞች ፎረም ቁጠባና የብድር አገልግሎት ህጋዊ ሰዉነት እንዲያገኝ በማድረግ ሴት ሠራተኞች ፎረም አባላት የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

167. የመ/ቤቱ የሠራተኞች ክበብ አገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻልና ክበቡን በማገዝ በተመጣጣኝ ዋጋ ለሠራተኛው የምግብ አገልግሎት እየቀረበ ከመሆኑም በተጨማሪ የተገዛው የዳቦ ማሽን አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ ለሠተራኛው በተመጣጣኝ ዋጋ ዳቦ በማቅረብ የኑሮ ዉድነቱን ጫና ለማገዝ ጥረት ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል መሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን ሠራተኛዉ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ በማድረግ ለሠራተኞች ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡

168. የነፃ ትምህርት ዕድል በማፈላለግ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የመ/ቤታችንን ሴት ሠራተኞች ተጠቃሚ ለማድረግ በተደረገው ጥረት በ2014 የመ/ቤቱ ዝቅተኛ ትምህርት ላላቸዉ ሴት ሰራተኞች 3 በዲግሪ እና 3 በዲፕሎማ በድምር 6 የመ/ቤቱ

ሠራተኞች በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን ቀድመዉ በትምህርት ላይ ለለሚገኙ 8 ሴት ሠራተኞች ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡

169. ኦዲተሮች የመስክ የሥራ ድልድል ሲደረግ ለሴት ኦዲተሮች ቅድሚያ በመስጠትና ምቹ የሆነ የሥራ ቦታ ምደባ እንዲያገኙ በማድረግ በስራ ስምሪት ድልድል ወቅት ቅድሚያ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

170. በዓለማችን የተከሰተውን የኮሮና ወረርሽኝ ለመከለከል እንዲሁም የሠራተኛወን ጤና ከመጠበቅ አንጻር ባለፈዉ አመት የተዘጋጀዉን የኮቪድ- 19 መከላከል ፕሮቶኮል መሰረት በማደረግ በዚህ አመትም በተቀመጠዉ ፕሮቶኮል መሰረት የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸዉ

የአቅም ግንባታ እና ከኦዲት ባለድርሻ አካላት ጋር የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ

171. በመ/ቤታችን ራሱን የቻለ የሥልጠና ተቋም ለመገንባት በ 5 ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ ይዞ ቅድመ ሁኔታዎችን እያመቻቸ የሚገኝ ሲሆን ለጊዜው በመ/ቤታችን የተዘጋጁ የሥልጠና ክፍሎችን በመጠቀም ሥልጠና እየተሰጠ ይገኛል፡፡

172. በዚህም መሠረት በመ/ቤቱ በ2014 ዓ.ም 49 ዓይነት የሥልጠና ፍላጎቶችን በመለየት በማኔጅመንት በማጸደቅ የሥልጠና ካላንደር እንዲዘጋጅ ተደርጓል፤ በፀደቀው ካላንደር መሰረትም ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

173. በዚህም መሰረት በ26 የተለያዩ የስልጠና ርዕሶች ላይ በገጽ ለገጽ ለ179 ሴቶች እና ለ318 ወንዶች በድምሩ ለ497 ሰራተኞች የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎች ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ ለ25 ሴት እና ለ44 ወንድ በድምሩ ለ69 ሰራተኞች በ8 የስልጠና ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተሰጠው ስልጠና በቨርቹዋል (Zoom) የተወሰደ ነው፡፡

174. በሌላ በኩል ለ42 የመ/ቤቱ ሠራተኞች የትምህርት ዕድሎች የተሠጠ ሲሆን በዚሁም መሠረት ሁለተኛ ዲግሪ አገር ውስጥ 1 ሴት፣ ውጭ ሀገር 1 ወንድ፣ ኤሲሲኤ (ACCA) ትምህርት 2 ሴቶችና 17 ወንድ በድምሩ 19 ሠራተኞች እየተማሩ የሚገኙ ሲሆን 1 ወንድ (ACCA) ትምህርት ያጠናቀቀ እንዲሁም በተጨማሪም IDI (INTOSAI Development Initiative) በሚሰጠዉ Professional Education for SAI-P (PESAI-P) የአንድ ዓመት ትምህርት በኦን ላይን (online) 20 ሠራተኞች በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡

175. በሌላ በኩል ለሌሎች አካላት አቅም ግንባታ ድጋፍ ከማድረግ አንጻር ለ4 ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች፣ ለ8 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች እንዲሁም ለመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ተሰጥቷል፡፡

የኦዲት ባለድርሻ አካላት የጋራ መድረክ እና መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግን በተመለከተ

176. በመንግስት ፋይናንስና ሂሳብ አያያዝ ወይም ኦዲት ዙሪያ የሚዘጋጅ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ የኢትዮጵያ አካዉንቲንግና ኦዲቲንግ ቦርድ ባዘጋጀዉ ሴሚናር ላይ ባለሙያ በመመደብ እና ጽሑፍ በማቅረብ ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡

177. ቋሚ ኮሚቴዉ በሚያዘጋቸዉ ይፋዊ ህዝባዊ ስብሰባ 13 እና በመስክ ጉብኝቶች 6 በድምሩ 19 መድረኮች ላይ በመገኘት በተነሱ ጉዳዮች ላይ ተገቢ ማስረጃ በመስጠት ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በመ/ቤቱ የተሰጡ የግንዘቤ ማስጨበጫዎች፣ ይፋዊ የዉያየይት መድረኮች፣ ከ40 በላይ የመ/ቤቱ የተለያዩ መድረኮችና ሁነቶች፣ የሚዲያ ዳሰሳ ውጤቶችን፣ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ጽሁፎች እንዲሁም 2002-2006 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት ቡክሌት እና የመ/ቤቱ የ76 ዓመታት ታሪካዊ መጽሐፍ ሶፍት ኮፒያቸው በድረ ገጽ በመጫንና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለህዝብ ተደራሽ ተደርጓል፡፡

የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ

178. ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል የኦዲት ባለሙያ 669፣ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ 344 እና 5 የበላይ አመራር በድምሩ 1018 የሰው ኃይል በ5 ዓመቱ የስትራቴጂክ እቅድ ዘመን የሚሟላ ተፈቅዷል፡፡ የኦዲት ሥራው በመጋቢት ወር 2013 ሲጀመር 473 ኦዲተሮችና 200 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 673 ሠራተኞች በሥራ ላይ ነበሩ፡፡ በኦዲት ዓመቱ ውስጥ 15 ሰራተኞች ለድጋፍ ዘርፍ ተቀጥርዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከስራ የለቁት በገዛ ፈቃዳቸዉ ከኦዲት 34 ከድጋፍ 12 በድምሩ 46 ሰራተኞች በጡረታ 10 በሞት 4 ባጠቃላይ 60 ሰራተኞች በተለያየ ምክንያት መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

179. በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ 442 የኦዲት ባለሙያዎች (293 ወንድ እና 149 ሴት)፣ 186 የድጋፍ ሰጪ (83 ወንዶችና 103 ሴቶች) ሠራተኞች 1 የበላይ ኃላፊ በአጠቃላይ 629 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ ነበሩ፡፡ ክፍት የሥራ መደቦችን ለማሟላት በየወቅቱ ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ቢሆንም ባለው የሠራተኛ ፍልሰት እና በደመወዝ ማናስ ምክንያት ችግሩን ማስወገድ አልተቻለም፡፡

የ2013 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም

180. ለ2013 በጀት ዓመት በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ መደበኛ በጀት ብር 96,648,980.00 የተፈቀደ ሲሆን ለዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ብር 90,583,725.00 (93.72%) መጠቀም ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሰየማቸው ገለልተኛ ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ለም/ቤቱ ተልኳል፡፡

2014 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም

181. ለ2014 በጀት ዓመት በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ መደበኛ በጀት ብር 115,905,746.00 የተፈቀደ ሲሆን ለዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ በዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ ለመጠቀም የተቀደ ብር 83,980,548.63 ሲሆን በዕቅዱ መሠረት ብር 77,723,522.77 (92.55%) መጠቀም ተችሏል፡፡ የተቀረው በጀት ብር 38,182,223.23 በቀሪ ወራት ውስጥ ለማከናወን ለታቀዱት ተግባራት ዕቅዱ መሠረት ሥራ ላይ የሚውሉ ይሆናል፡፡

ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በተመለከተ

182. የመ/ቤቱ ሥራዎች በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የኦዲት አሠራር የሚያዘምኑና የመ/ቤቱን የመረጃ ስርዓቶች ተመጋጋቢ እንዲሆኑ የሚያደርጉ የመ/ቤቱን ሥራ ከማቀላጠፍ፣ ወረቀት አልባ ተቋም ለማድረግና ባለፉት አመታት ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ የኦዲቱን ስራ በሲስተም በማገዝ ምቹ እና ቀላል ለማድረግ ስራዎቻችንን በቴክኖሎጂ የማዘመን ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮና የተወሰዱ እርምጃዎች

183. በአፈጻጸም ወቅት መ/ቤቱን ካጋጠሙት ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር የመረጃ ሥርዓት (IFMIS) መቆራረጥ፣ በፀጥታና በኮሮና ወርሽኝ ምክንያት ሥራዎችን በታቀደው ዕቅድ መሠረት ማጠናቀቅ አለመቻል፣

184. የተዋሃዱ እና የፈረሱ መ/ቤቶች ኃላፊዎች መቀያየር ምክንያት በወቅቱ ከኦዲት ተደራጊዎች መረጃ በተጠየቁ ጊዜ ማቅረብ አለመቻል፣

185. ለኦዲት ተደራጊዎች ለተላከው ፋክት ሽት እና ለረቂቅ ሪፖርት በወቅቱ ምላሽ አለመስጠት፣ የመ/ቤት ኃላፊዎችን በተለያዩ ምክንያቶች ማግኘት ባለመቻሉ የመውጫ ስብሰባ በተጠየቀው ጊዜ ውስጥ ማድረግ አለመቻል፣ እንዲሁም ከመውጫ ስብሰባ በኋላ በርካታ ዶክመንቶች አሉን በማለት ለማጣራት ተጨማሪ ጊዜ በመውሰዱ ኦዲቱ በወቅቱ እንዳይጠናቀቅ ችግር መሆን፣

186. የሂሳብ ሪፖርቶችን በወቅቱ ዘግቶ አለማቅረብ፣ የሥራ ቢሮና የሂሳብ ዶክሜንቶች በተቀመጠ ጊዜ ገደብ ዉስጥ ተዘጋጅቶ ለኦዲት ሥራ አለማድረስ፣ ለሥራ የሚያስፈልጉ ማህበራዊ ርቀትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ምቹ የሥራ ቢሮና የሂሳብ ሰነዶችን በወቅቱ ማቅረብ አለመቻል፣

187. ካለው የኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች ከመ/ቤቱ ተጠንቶ የቀረበው መዋቅር ከደመወዝ ጋር ቢሆንም በታህሳስ 17/2012 መዋቅር ብቻ ፀድቆ ደመወዙ ባለመፅደቁ የዝቅተኛ ሠራተኞችም መነሻ ደመወዝ ከሲቪል ሰርቪስ ጣሪያ ወለል በታች በመሆኑ እንዲሁም ከመዋቅሩ ጋር አብሮ መስተካከል ያለበት ደመወዝ አለመፈቀዱ በመ/ቤቱ ሠራተኞች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከመድረሱም በላይ ከፍተኛ የባለሙያ ፍልሰት ማስከተሉ፤ ለዚህም የተከበረው ምክር ቤት ትኩረት እንዲሰጥ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

188. ከአንድ ዓመት በፊት በስራ ላይ የነበሩት 3 የበላይ ኃላፊዎች መካከል 2ቱ የሥራ ጊዜያቸውን ጨርሰው የተሰነበቱ በመሆኑ ስራው ከ1 ዓመት በላይ በ1 ኃላፊ ብቻ እየተመራ በመሆኑ ከፍተኛ የሥራ ጫና መፍጠሩ፣

189. ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ከሚመለከታቸዉ የስራ ሃላፊዎች ጋር በመነጋገር ለመፍታት ጥረት ተደርጓዋል፡፡ ያልተፈቱ ችግሮች ቢኖሩም ችግሩን በመቋቋም

ስራዎቻችንን በአቀድነው መሰረት ጥሩ በሚባል አፈፃፀም ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ የሰራተኛ ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም ከመዋቅሩ ጋር እንዲፈቀድ የተጠየቀዉ በከፊል የተመለሰ ቢሆንም ችግሩን በሚፈታ እና ሁሉንም ያማከለ ባለመሆኑ በሰራተኛዉ ላይ ቅሬታ የፈጠረ በመሆኑ የዚህን መቤ/ት ጥያቄ መመለስ ትንሽ ሰጥቶ ብዙ የሚተረፍበት በመሆኑ የተከበረዉ ም/ቤት ጉዳዩን በአንክሮ አይቶ ምላሽ እንዲሰጥበት በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

190. በሌላ በኩል ለኦዲተሮች በመስክ ስራ ላይ በሚቆዩበት ጊዜ የሚከፈለው ውሎ አበል አነስተኛ በመሆኑ ከኑሮ ውድነቱ አንጻር በቂ ባለመሆኑ ጫና መፍጠሩ፣ በተጨማሪም የሰራተኞች መነሻ ደመወዙም ከሲቪል ሰርቪሱ ደመወዝ ወለል በታች መሆኑ ይህም ታይቶ ለችግሩም ትኩረት በመስጠት የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲሰጥ የተከበረውን ምክር ቤት በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

191. በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ሀላፊነታቸውን የተወጡትን ሰራተኞች በም/ቤቱ ፊት ላመሰግናቸው እወደለሁ፡፡

የ2014/15 ኦዲት ዓመት ዕቅድ

192. የመ/ቤቱ የ5 ዓመት የሚተገበር አዲስ ስትራቴጅክ ዕቅድ በቴክንክ ኮሚቴ፣ በስትርንግ ኮሚቴ፣በማናጅመንት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ተገምግሞና አስታየት ተሰጥቶበት ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡ በዚህም መሠረት በ2014 በጀት ዓመት በጀት ከተመደበላቸው 179 የፌዴራል መ/ቤቶች እንዲሁም 54 ቅርንጫፎች ውስጥ ቀደም እንዳሉት ዓመታት 14 የሚሆኑት ሂሳባቸው በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እንደሚደረጉ ታሳቢ ተደርጎ የተቀሩትን 165 መ/ቤቶች 54 ቅርንጫፎች በመ/ቤታችን ኦዲት በማድረግ የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ሽፋኑን 100% ለማድረስ ታቅዷል፡፡ እንደዚሁም ከመጋቢት 2014 እስከ ጥር 2015 ድረስ ባለው ጊዜ 24 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችን እና 6 ክትትል ኦዲቶችን በማከናወን 30 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም በ316 የመሠረታዊ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ወረዳዎችና የሴክተር ቢሮዎች 268 የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ ለማከናወን እና 47 የማረጋገጥ ስራዎች (Verifications); እንደዚሁም አንድ ፕሮግራም አቀፍ ኦዲት በገንዘብ ሚኒስቴር ደረጃ ለማካሄድ በእቅድ ተይዟል፡፡

በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና

በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት

193. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ኃላፊነት ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የእርዳታ ሂሳቦችን በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት አስፈላጊው የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊ ድርጅቶች እና ለተቆጣጣሪ መ/ቤቶች አስፈላጊው ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

194. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በ2013 በተከናወኑና ለመ/ቤታችን የደረሱ ኦዲቶች ላይ የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 2 ክፍል 3 በዝርዝር የቀረበ ስለሆነ ዝርዝሩን ከዚያው መመልከት ይቻላል፡፡

የመንግስት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ኦዲት ክትትል

195. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑና ከሚያዝያ 1/2013 እስከ መጋቢት 30/2014 ዓ.ም ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 37(የተለያዩ ዓመታት በጀት ዓመት ሪፖርትን በመቁጠር) ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በልማት አጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 190 በድምሩ 227 (ይህ ቁጥር በበጀት ዓመቱ የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ ድርጅት ወይም ፕሮጀክት እያንዳንዱን ሪፖርት በመቁጠር የተወሰዱ) ናቸው፡፡

196. ለመ/ቤታችን የደረሱት የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ሲተነተኑ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 143፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 49፣ የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ

አስተያየት የተሰጣቸው (Adverse Openion) 1፣ አቋም ለመውሰድ የማይቻል በመሆኑ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 30፣ የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠበት ኢንቲሪም ኦዲት 4 በድምሩ 227 ናቸው፡፡

የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

197. ኮርፖሬሽኑ በ2013 በጀት ዓመት ከኦዲት ሥራ አገልግሎት ብር 46,888,321 ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር 43,920,309 ገቢ ያገኘ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ ብር 34,055,916 ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር 30,241,177 ወጪ ያደረገ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ ብር **9,575,392** የተጣራ ትርፍ ሊያገኝ ችሏል፡፡

ማጠቃለያ

198. የ2013 በጀት አመት ሂሳብ ላይ የተካሄደዉ የፋይናነስ እና ህጋዊነት ኦዲት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የታቀዱትን ጨምሮ በወቅታዊ ሁኔታ ከተቋረጡት ስድስት መ/ቤች እና አራት ቅርንጫፎ በስተቀር በተቀሩት የፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲቱ ተከናዉኗል፡፡ አፈጻጸሙም 96.6%

199. በሌላ በኩልም የክዋኔ ኦዲትን እቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ 25 አዲስ፣ ከአምናዉ የዞረ 1 ኦዲት እና 4 የክትትል ኦዲት በድምሩ 30 ለመስራት ታቅዶ የ24 ኣዳዲስ ከባለፈዉ አመት የዞረዉ አንደ ኦዲት ተጨምሮ 25 እና 4 የክትትል ኦዲት በድምሩ የ29 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ወጪ ተደርግዋል አፈጻጸሙ 96.67% ብቻ ሆንዋል፡፡አንድ ኦዲት ኦዲት ተደራጊዉ በወቅቱ ቢሮ ባለማቅረቡ እና ለኦዲት ማስታወሻዎች በወቅቱ ምላሽ ባለመስጡ የኦዲት ስራዉ በታቀደዉ ግዜ ሊጠናቀቅ አልቻለም፡፡

200. የ2013 በጀት አመት የኦዲት ዉጤት ሲታይ ነቀፌታ የሌለበት፣ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነዉ የተገኙ ላይ መሻሻል የታየ ሲሆን፣ አስተያየት መስጠት ያልተቻለባቸዉ እና የጎላ ችግር ያለባቸዉ ሆኖ በመገኘታቸዉ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸዉ መሻሻል ያልታየበት ሁኖ ቀጥሏዋል፡፡

201. የግኝቶቹም ባህሪ ሲታይ የመጨመር እና የመቀነስ ጉዳይ ካልሆነ በቀር እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ የ2013 በጀት አመትም ዋነኛ ሁነዉ የቀጠሉት የጥሬ ገንዘብ እና

የባንክ ሂሳብ አያያዝ፣ የዉዝፍ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ አለመሰብሰብ እና አለማወራረድ በተለይ ከእስካሁኑ አመት በተለዬ ተሰብሳቢ ሂሳብ ሂሳብ በጣም ጨምሮ የታዬ መሆኑ፣ በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት አለመሰብሰብ፣ ደንብ እና መመሪያዎች ያልጠበቁ ግዢዎችን የዉስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም የበጀት አስተዳደር እና አጠቃቀም በብልጫ የተከፈለ ክፍያዎች የመንግስት ንብረት አጠቃቀም እና አስተዳደር የሚታየ ጉድለቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡ በሌላ በኩልም በበጀት አመቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በተደረገ ክዋኔ ኦዲቶች በርካታ ሊዘረጉ የሚገባ የአሰራር ስርዓቶች የየመ/ቤቶቹን ቅልጥፍና እና ዉጤታማነት እንዲሁም ለተልእኮ ስኬት አስተዋጽኦ የነበሩ የህግ እና የአሰራር ስርዓቶች እንዲሁም ተዘርግተዉ የማይተገበሩ የአሰራር ስርዓቶች በመ/ቤት ዉስጥም ሆነ ከሌሎች ተቅዋማት ጋር የቅንጅት እና የትብብር ጉድለቶች ዋና ዋና ግድፈቶች ሆኖ ተገኝቷል፡፡

202. በዚሁ መሰረትም የፋይናንስና ህጋዊነት ሆነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ጉድለቶችን ከማሳየት ባሻገር የታዩ የአሰራር ጉድለቶች እና ክፍተቶችን ለማረም እና ለማስተካከል የሚያስችሉ የመፍተሄ ሃሳቦችን ጭምር ያካተቱ ከመሆኑም በላይ አብዛኛዎቹ የተሰጡት ማሻሻያ ሃሳቦች በኦዲት ተደራጊዎችም ጭምር ስምምነት የተደረሰባቸዉ ናቸዉ፡፡

203. ስለዚህ ዝርዝር የፋይናንስ እና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቱ አጠቃላይ ዘገባ በሁለት ጥራዝ እንዲሁም የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርቶች አስተያየት ሊሰጥባቸዉ ያልተቻለ የፋይናንስ እና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቶች እና ተቀባይነት የሚያሳጣ አሰተያየት የተሰጣቸዉ መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርቶች አንድ ላይ ተደራጅተዉ በሲዲ ለተከበሩ አፈጉባዔ የተላኩ በመሆኑ ሪፖርቶቹን የም/ቤቱ የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጠር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታችሁ ቋሚ ኮሚቴዎች ጭምር በጥልቀት ታይተዉ እና ተመርምረዉ ተገቢዉ እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል እና ግፊት ሊደረግ ይገባል፡የተጠያቂነትን ስርዓት ከማረጋገጥ አንጻር ፡የመንግሰት ወጪ አሰተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም የጀመረዉን ግልጽ ይፋዊ መድረክ አጠናክሮ እዲቀጥልበት በአክብሮት እየጠየኩ የገ/ሚ/ርም የጀመረዉን አስተዳደራዊ አርምጃ አጠናክሮ እንዲቀጥልበት

በዚሁ አጋጣሚ መለክቴን ላስተላለፍ እወዳለሁ ፡፡ በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በተተለያዩ ምክንያት ኦዲታቸው የተቋረጠ መ/ቤቶች

	በጸጥታ ችግር ምክንያት የኦዲት ስራው የተቋረጠ
	የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች
1	ደንቢዶሎ ዩንቨርስቲ
2	ወልዲያ ዩንቨርስቲ
3	ወሎ ዩኒቨርሲቲ፣
4	መቅደላ ዩኒቨርሲቲ፣
	የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች
1	**የገቢዎች ሚኒስቴር**
1.1	የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት
2	**የጉምሩክ ኮሚሽን**
2.1	የጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት
2.2	የአሶሳ ቅ/ጽ/ቤት
2.3	የሰመራ ቅት/ቤት
	ንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች
	ለኦዲተሮች ቢሮ ባለመስጠታቸው ኦዲት ያልተደረገ
1	የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝ3ባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት
	የሂሳብ ሪፖርት ባለመቅረቡ ኦዲቱ የተቋረጠ
1	የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን

አባሪ 2

በ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት እና ባለፉት ተከታታይ ሁለት ኦዲቶች

ሀ/	ሂሣባቸው የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው /Adverse opinion/	X
ለ/	አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች /Disclaimer Opinion/	XX
ሐ/	ከጥቂት ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሒሳባቸው አጥጋቢ በመሆኑ ነቀፌታ ያለበት (Except for) የተሰጣቸው	E

ተ.ቁ		የመ/ቤት ስም	ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት		
			2011	2012	2013
X	XX	**ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት**			
1	1	ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
2	2	ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ			X
3	3	ጂንካ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
4	4	ጅጅጋ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
5	5	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
6	6	ሚዛን ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
7	7	ወለጋ ዩኒቨርሲቲ			X
8	8	ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
9	9	ሀረማያ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
10	10	መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ			X
11	11	የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚ/ር			X
		የፋይናንስና ኮሚዩኒኬሽን መ/ቤቶች			
12	1	የቀድሞ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	X	X	XX
13	2	ብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮምሽን	X	XX	XX
14	3	ቱሪዝም ኢትዮጵያ		XX	X
15	4	የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	X	X	X

ተ.ቁ		የመ/ቤት ስም	ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት		
16	5	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር	E	X	X
17	6	የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት		XX	X
18	7	ማእከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ	E	X	X
19	8	የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ			X
20	9	የቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን		X	X
21	10	የኢትዮጲያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን	X	XX	X
		የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች			
22	1	የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን			XX
23	2	የሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል		XX	XX
24	3	የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት			XX
25	4	የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪግ ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ባለስልጣን			X
26	5	የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት			X
27	6	የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ		X	X
28	7	የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር			X
29	8	የስትራቲጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩት			X
30	9	የሰላም ሚኒስቴር			X
		የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች			
31	1	የኢኖቬንሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	X	XX	XX
32	2	የኢትዮጵያ ቴክኒካል ዩኒቨርስቲ			XX
33	3	የመቱ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
34	4	የብሂራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት	E	X	X
35	5	የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ልማት ማዕከል			X
36	6	የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት			X
37	7	የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
38	8	የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት			X
39	9	የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ	XX	X	X
40	10	የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ	X	X	X
41	11	አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
42	12	የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ	XX	X	X
43	13	የፌዴራል የፍትህና የህግ ምርምርና ስልጠና ኢንስቲትዩት			X
44	14	የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X

ተ.ቁ		የመ/ቤት ስም	ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት		
		የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች			
45	1	የቅዱስ ጴጥሮስ ቲቪ. ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል			X
46	2	ኤካ ኮተቤ የአዕምሮ ህክምናና አጠቃላይ ሆስፒታል			X

አባሪ 3

የተከናወኑ ልዩ ኦዲቶች

<table>
<tr><th rowspan="2">ተ.ቁ</th><th rowspan="2">የልዩ ኦዲት ስራዎች</th><th colspan="2">ምርመራ</th></tr>
<tr><th>የተጠናቀቀ</th><th>በሂደት ላይ ያለ</th></tr>
<tr><td>1</td><td>በገንዘብ ሚኒስቴር እና ኤ.ቢ.ሲ ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል በ2000 የሚሊኒየም በዓልን ለማክበር የ152 ተሽከርካሪዎች ግዥን በተመለከተ</td><td>✓</td><td></td></tr>
<tr><td>2</td><td>ቤተዛታ የጤና አገልግሎት ኃ/የተ/የግ/ማህበር የውስጥ ደዌ ልዩ ማዕከል የጥሬገንዘብ ጉድለትን በተመለከተ</td><td>✓</td><td></td></tr>
<tr><td>3</td><td>በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ</td><td>✓</td><td></td></tr>
<tr><td>4</td><td>በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት</td><td>✓</td><td></td></tr>
<tr><td>5</td><td>የአዲስ የመለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበር</td><td>✓</td><td></td></tr>
<tr><td>6</td><td>ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ግሽ አባይ ካምፓስ</td><td>✓</td><td></td></tr>
<tr><td>7</td><td>መርከብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን</td><td>✓</td><td></td></tr>
<tr><td>8</td><td>በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት</td><td>✓</td><td></td></tr>
<tr><td>9</td><td>ደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት የ2006 እና 2007</td><td>✓</td><td></td></tr>
<tr><td>10</td><td>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ኢትዮ-ኢንጅነሪንግ ግሩፕ (የቀድሞ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን) የተለያዩ መጠን ያላቸውን አውቶማቲክ ኢንቴሊጀንት ኢነርጂ ሜትሮችን አምርቶ ለማቅረብ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር የገባውን ውል እና ሥራውን በተመለከተ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የገባውን ውልና</td><td>✓</td><td></td></tr>
</table>

ተ.ቁ	የልዩ ኦዲት ስራዎች	ምርመራ	
		የተጠናቀቀ	በሂደት ላይ ያለ
11	በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ አዳማ የግብርና ማሽነሪ ማምረቻ ኢንዱስትሪ (የቀድሞ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን የአዳማ እርሻ መሳሪያዎች ኢንዱስትሪ) የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ	✓	
12	የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል		✓
13	የቀድሞ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን አሁኑ ኢትዮ-ኢንጅነሪንግ ግሩፕ		✓
14	የስኳር ኮርፖሬሽን		✓
15	የአደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን ለኤልሻዳይ ግብረ-ሰናይ ድርጅት በሰጠው ድጋፍ		✓
16	በመንገድ ፈንድ ጽህፈት ቤት የኩፖን ሽያጭ		✓
17	የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ		✓
18	የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት የሰርቨር ግዥን		✓
19	የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት		✓